# አዋጅ ቁጥር…./2013

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የካፒታል ገበያ አዋጅ

ካፒታል በማሰባሰብ፣ የገንዘብ ስርዓቱን በአዳዲስ ፈጠራዎች በመደገፍ እና የኢንቨስትመንት ስጋቶችን የመጋራት አሰራርን በማስፋፋት የአገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት የሚደግፍ የካፒታል ገበያ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ እና ገበያው ፍትሃዊ፣ ተአማኒ እና ቀልጣፋ እንዲሆን የሚያስችል የቁጥጥር እና በበላይነት የመከታተል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣

ከሕዝብ ካፒታል ለመሰብሰብ የሚፈልጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጭዎች የሚገዙበትን ወጥ የሆኑ መስፈርቶች በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በሀገሪቱ የፋይናንስ ስርዓት ላይ የሚፈጠሩ መዋቅራዊ ስጋቶችን ለመለየት፣ ለመከላከል፣ እና ለመቀነስ በካፒታል ገበያ ላይ ጠንካራ የቅርብ ክትትል እና የቅኝት ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው አዋጅ ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ ‹‹የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር …./2013›› ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ ‹‹**ማስታወቂያ**›› ማለት

ሀ) በጽሁፍ፣ ማስታወቂያ በመለጠፍ፣ ወይም በሰርኩላር ወይም በሌሎች ሰነዶች፤

ለ) በፎቶግራፎች፣ በሲኒማቶገራፊ ፍልሞች ወይም ቪዲዮ አወደ-ርዕይ፤

ሐ) በድምጽ ስርጭት፣ በቴሌቪዢዮን፣ ወይም ቀረጻዎችን በማሰራጨት፤ ወይም

መ) እንደ ድረ-ገጽ እና ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ባሉ ሌሎች ኤሌክተሮኒክ የመገናኛ ብዙሃን መድረኮች፤

የሚተላለፉ ማስታወቂያዎችን ያካትታል፡፡

2/ ‹‹**ተሿሚ እንደራሴ**›› ማለት በባለስልጣኑ የንግድ ፈቃድ የተሰጠውን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በመወከል ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት የሚያከናውን ሰው ነው፡፡

3/ ‹‹**በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች**›› ማለት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሆነው የሚያስገኙት የገንዘብ ፍሰት በዋናነት ተለይተው በሚታወቁ የተሰብሳቢ ወይም ሌሎች የገንዘብ ሰነዶች፣ ቋሚ ወይም ተዘዋዋሪ የሆኑ፣ በውል በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ገንዘብ የሚለወጡ፣ በተጨማሪም እነዚህን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለያዛቸው ሰው የሚከፈለው ገንዘብ በወቅቱ እንዲፈፀም ለማረጋገጥ ዋስትና የተደረጉ ማንኛውም መብቶች ወይም ሌሎች ሃብቶች፣

ለ) አክሲዮኖችን ወይም ከጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች የሚገኙ መብቶችን ሳይጨምር ነገር ግን የተስፋ ወረቀቶችን ጨምሮ ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣

ሐ) ሊሸጡ እና ሊለወጡ የማይችሉ ሰነዶችን ሰብስቦ እንዲሸጡ እንዲለወጡ ወይም በራሳቸው ለግብይት የማይውሉ ሰነዶች የግብይት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መፍጠር ሂደትን ተከትሎ በተቋቋመ ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም ሃብት ላይ ከሚጠራቀም ዋና ብድር ወይም ወለድ፣ ገቢ፣ የካፒታል ክፍፍል ወይም ክፍያዎች ወይም በእነዚህ ተቋማት ላይ ድርሻ የያዙ ባለሃብቶች ማንኛውም መብት ወይም ጥቅም፣ የዕዳ ሰነድ ወይም ህጋዊ የአላባ ተጠቃሚነት ወይም በድርሻ ላይ የጥቅም መብቶችን የሚያረጋግጡ የምስክር ወረቀቶች፣ ወይም

መ) ሌላ ማንኛውም በሀብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ነዋይ አይነት መብት፣ ጥቅም ወይም ሰነድ፡፡

4/ ‹‹**ባንክ**›› ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ ስራ እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም በመንግስት ባለቤትነት ስር ያለ ባንክ ማለት ነው፡፡

5/ ‹‹**ደላላ**›› ማለት ኮሚሽን እያስከፈለ በሌሎች ስም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመሸጥ እና የመግዛት ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፡፡

6/ ‹‹**የካፒታል ገበያ**›› ማለት እንደ አክሲዮን፣ ቦንድ፣ ተዛማጅ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም እነዚህን የመሰሉ የተለያዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የሚደረግበት ገበያ ነው፡፡

7/ ‹‹**የካፒታል ገበያ ተዋናዮች**›› ማለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች፣ ኢንቨስተሮች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያዎች ናቸው፡፡

8/ ‹‹**የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ**›› ማለት ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ስራዎች ላይ የተሰማራ ሰው ነው፡፡

9/ ‹‹**ማዕከላዊ የክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ወገን**›› ማለት

ሀ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይቶች ላይ ድህረ ግብይት የማጣራት እና ክፍያ የመፈጸም ስራን፣ እና

ለ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተገበያዮች መካከል የተቃራኒ ወገን ስጋትን የመውሰድ ስራን የሚመለከት ነው፡፡

10/ ‹‹**ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት**›› ማለት፡-

ሀ) ከተማከለ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አያያዝ ጋር በተገናኘ፡-

1) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወጥነት ባለው መንገድ የሚከማቹበት፣ ወይም ወደ ኤሌክትሮኒክ ይዘት ተቀይረው የሚቀመጡበት፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአውጪው ኩባንያ ወይም በአውጪው ኩባንያ ስም ሆኖ

በሚሰራ ሌላ ኩባንያ ስም የሚመዘገቡበት ሆኖ እነዚህ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በተመለከተ የሚደረግ ግብይት ሰነዶቹን በአካል ማረካከብ ሳያስፈልግ የሰነዶቹ መተሳሰቢያ መዝገብ ላይ ብቻ በሚደረግ ወጪና ገቢ ለማስተላለፍ የሚያስችል ስርዓት፣ ወይም

2) በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ሂደት ወቅት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ፣ ክፍያና እና ርክክብ ያለ አካላዊ ቅብብል ለማከናወን የሚያስችል ወይም ግብይቱን የሚያሳልጥ ዘዴ ወይም ስርዓት፤ እና

ለ) ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ድጋፎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሰጥ ስርዓት ነው፡፡

11/ ‹‹**የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ**›› ማለት

ሀ) ሰዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም ሌሎች ንብረቶችን በባለቤትነት በመያዝ፣ በይዞታ በማቆየት፣ በማስተዳደር፣ ወይም በማስተላለፍ ገቢ ወይም ትርፍ ለማግኘት የሚሳተፉበት ወይም ይህን ዓይነት ዓላማ ወይም ውጤት ለማስገኘት ታስቦ የተቋቋመ ወይም ከእንደዚህ ዓይነት አሰራር ከሚገኝ ገቢ ወይም ትርፍ የሚከፈልበት የስምምነት መዋቅር፤

ለ) በስምምነት መዋቅሩ ውስጥ የሚሳተፉ ኢንቨስተሮች የጋራ ማዕቀፉ ሀብቶች የዕለት-ተለት አስተዳደር ቁጥጥር የማይዙበት፤ እና

ሐ) የፈንዱን ሀብቶች የሚያስተዳድረው ሰው የፈንዱን ሀብት እና የአባላቱን ሂሳቦች በኃላፊነት የሚያስተዳድርበት

ነው፡፡

12/ ‹‹**የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኝ**›› ማለት ለአንድ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ የስራ አመራር እና አፈጻጸም አጠቃላይ ኃላፊነት ያለበት ተቋም ነው፡፡

13/ ‹‹**ኩባንያ**›› ማለት በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመ የአክሲዮን ኩባንያ ነው፡፡

14/ ‹‹**ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት**›› ማለት የአንድን ተቋም፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጭ ብድርን የመመለስ አቅም በተመለከተ ተቀባይነት ያላቸው እና የታወቁ የመመዘኛ መስፈርቶችን በመጠቀም የሚሰጥ አስተያየት ነው፡፡

15/ ‹‹**ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በተሰጠ የባለስልጣኑ ፈቃድ ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት የሚሰጥ ሰዉ ነዉ፡፡

16/ ‹‹**ጠባቂ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የደንበኞችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለጥበቃ ዓላማ ወይም ለምቹ አያያዝ ሲባል በይዞታው ስር የሚያስቀመጥ የገንዘብ ተቋም ነው፡፡

17/ ‹‹**ቀናት**›› ማለት በኢትዮጵያ ካላንደር መሠረት ከቅዳሜ፣ ከእሁድ እና ከሕዝብ በዓላት ውጭ ያሉ ቀናት ማለት ነው፡፡

18/ ‹‹**የገበያ አከናዋኝ**›› ማለት በሙሉ ጊዜው ወይም በትርፍ ጊዜው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ እንደ ወኪል፣ ደላላ፣ ወይም ራሱ ተገበያይ ሆኖ በሌላ አካል የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሽያጭ በማቅረብ፣ ለግዥ በማቅረብ ወይም በግብይት ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

19/ ‹‹**በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መገበያየት**›› ማለት ለራስ ወይም ስለ ሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን፡-

ሀ) መሸጥ ወይም መግዛት፣
ለ) ማውጣት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ፣
ሐ) ማስቀመጥና መጠበቅ፣
መ) ክፍያ ማጣራትና መፈጸም፤
ሠ) ማበደር ወይም ማስያዝ፣ ወይም
ረ) ሌላ ማንኛውም ባለስልጣኑ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ የሚደረግ ግብይት ነው ብሎ የሚወስነው ስራ ነው፡፡

20/ ‹‹**የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**›› ማለት ማንኛውም በኩባንያ የሚወጣ ወይም ሊወጣ የታቀደ የዕዳ ሰነድ፣ ዋስትና ያለው የዕዳ ሰነድ፣ የብድር ስቶክ፣ ቦንድ፣ ወይም የተስፋ ሰነድ ሆኖ ባለዕዳነትን የሚፈጥር ወይም የሚያረጋግጥ ነው፡፡

21/ ‹‹**ግዑዝ-አልባ ማድረግ**›› ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማውጣት እና መመዝገብ ነው፡፡

22/ ‹‹**ግዑዝ-አልባ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**›› ማለት የሰነዱ ባለቤትነት በኤሌክትሮኒክ የምዝገባ ደብተር ባለቤትነትን በማስገባት ብቻ የሚረጋገጥበት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ነው፡፡

23/ ‹‹**ተዛማጅ**›› **ወይም** ‹‹**ተዛማጅ ውል**›› ማለት ዋጋው ከሌላ መሠረታዊ ከሆነ እንደ አክሲዮን፣ ቦንድ፣ ወይም ምርቶች እና ገንዘቦች ያሉ ሀብቶች የሚመነጭ ሆኖ እንደ አክሲዮን ወይም ሌላ የገንዘብ ሰነድ የሚሸጥ፣ የሚገዛ ወይም ግብይት የሚደረግበት ገንዘብ ነክ ሰነድ ነው፡፡

24/ ‹‹**የተዛማጅ ውሎች ገበያ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በገበያው ተመዝግበው ግብይት ሊደረግባቸው የሚችሉ ተዛማጅ ውሎች እንዲመዘገቡበት በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ወይም ለዚሁ ዓላማ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት ይሁንታ የተሰጠው ገበያ ነው፡፡

25/ ‹‹**የውጭ ኦዲተር**›› ማለት የኦዲት አገልግሎት እንዲሰጥ በሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ የተሰጠው ገለልተኛ ኦዲተር ነው፡፡

26/ ‹‹**ሀሰተኛ መረጃ**›› ማለት በአቀራረቡ እና በተገለጸበት አውድ ውስጥ ሲታይ አሳሳች የሆነ አገላለጽ ሲሆን በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ ሳይካተት የቀረ ወይም ሆን ተብሎ ኢንቨስተሮችን ወይም የገበያ ተሳታፊዎችን ለማሳሳት የተገለጸን ማንኛውም በጽሁፍ የቀረበ ነገርን ይጨምራል፡፡

27/ ‹‹**የገንዘብ ሰነዶች**›› ማለት በተዋዋዮች መካከል የሚደረጉ፣ የሚሻሻሉ፣ ግብይት እና ክፍያ የሚደረግባቸው ገንዘባዊ ይዘት ያላቸው ውሎች ናቸው፡፡

28/ ‹‹**የውጭ አገር ኢንቬስተር**›› ማለት እንደ ኢትዮጵያዊ መቆጠር የሚፈልግ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ አገር ዜጋን ሳይጨምር በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ አገር ካፒታል በስራ ላይ ያዋለ ሆኖ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-
ሀ) የውጭ አገር ዜጋ፤
ለ) የውጭ አገር ዜጋ የባለቤትነት ድርሻ የያዘበት ድርጅት፤
ሐ) ከኢትዮጵያ ውጭ በማንኛውም ኢንቬስተር የተመዘገበ ድርጅት፤
መ) በ ‹ሀ›፣ ‹ለ› እና ‹ሐ› ከተጠቀሱት ኢንቬስተሮች በሁለቱ ወይም በሦሥቱ በጋራ የተቋቋመ ድርጅት፤ ወይም

ሠ) እንደ ውጭ አገር ኢንቬስተር መስተናገድ የመረጠ በቋሚነት በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ፡፡

29/ ‹‹**መንግስት**›› ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ነው፡፡

30/ ‹‹**ሰነድን ማስቀመጥ**›› ማለት በወረቀት መልክ ያለን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የምስክር ወረቀቶች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በማስቀመጥ የሰነዶቹ ዝውውር በሂሳብ መዝገብ ለውጥ ብቻ እንዲከናወን ማስቻል ነው፡፡

31/ ‹‹**ተቀማጭ የተደረገ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**›› ማለት የመሠረታዊው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የምስክር ወረቀት በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት እንዲመዘገብና እንዲቀመጥ የተደረገ ሰነድ ነው፡፡

32/ ‹‹**የመጀመሪያ ዙር የሕዝብ ሽያጭ**›› ማለት

ሀ) አስቀድሞ የኩባንያው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሕዝብ በሽያጭ ባልቀረቡበት ሁኔታ፤ ወይም

ለ) አስቀድሞ ለህዝብ በሽያጭ የቀረቡት የኩባንያው አክሲዮኖች ከጊዜ በኂላ ሙሉ በሙሉ በኩባንያው ተመልሰው በተገዙበት ሁኔታ፣

ማንኛውንም የአንድ ኩባንያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሕዝብ ለመሸጥ ማቅረብ ነው፡፡

33/ ‹‹**ኢንቨስተር**›› ማለት ትርፍ ለማግኘት ሲል በዚህ አዋጅ መሰረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የሚገዛ፣ የሚሸጥ ወይም የሚይዝ ማነኛዉም ሰዉ ነዉ፡፡

34/ ‹‹**የኢንቨስትመንት ባንክ**›› ማለት ተቀማጭ ገንዘብ የማይሰበስብ የገንዘብ ተቋም ሆኖ በሌሎች ኩባንያዎች፣ በመንግስት ወይም በሌላ ተቋም የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በውክልና በመሸጥ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪውን ከገዢ ሕብረተሰብ ጋር በማገናኘት ካፒታል በማሰባሰብ፣ የኩባንያዎችን ውህደት እና ዳግም መልሶ የማዋቀር ስራዎችን በማገዝ፣ ለደንበኞቹ እንደ ደላላ እና ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የአማካሪነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

35/ ‹‹**ኢንቨስትመንት**›› ማለት ቀጥለው የተዘረዘሩትን ያካትታል፡-

ሀ) ለህዝብ በሽያጭ የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣

ለ) በውጭ አገር የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም የግብይት መድረክ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት በተፈቀደ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለ የባለቤትነት ድርሻ ወይም ክፍልፋይ፣

መ) ከላይ የተጠቀሱ ዓይነት የባለቤትነት ድርሻዎችን ወይም ክፍልፋዮችን እና ሌሎች መሰል ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት የተመደቡ ገንዘቦች፣ ወይም

ሠ) ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በባለስልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ኢንቨስትመንት ነው ተብሎ የተፈረጀ ሌላ ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይን፡፡

36/ ‹‹**የኢንቨስትመንት አማካሪ**›› ማለት ፈቃድ ተሰጥቶት እና

ሀ) ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ሌሎችን የማማከር ስራ የሚሰራ፤

ለ) ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ ሪፖርቶችን እና ትንተናዎችን የማውጣት እና የማሰራጨት ስራን መደበኛ ስራው አድርጎ የሚሰራ፤ ወይም

ሐ) እንደ ቦንድ፣ ምርት፣ የጋርዮሽ ገንዘብ እና አክሲዮን በመሳሰሉ የተወሰኑ የኢንቨስትመንት ዓይነቶች ላይ የተለየ ፈቃድ ተሰጥቶት በገንዘብ ነክ እና በኢንቨስትመንት ጉዳዮች ላይ ምክር የሚሰጥ

ሰው ነው፡፡

37/ ‹‹**አውጪ**›› ማለት መንግስት፣ ኩባንያ ወይም ሌላ ሕጋዊ ድርጅትን ጨምሮ ማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለሽያጭ የሚያወጣ፣ ወይም ለማውጣት መዘጋጀቱን የሚያስተዋውቅ ሰው ነው፡፡

38/ ‹‹**ፈቃድ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ባለስልጣኑ ለአንድ ሰው በማንኛውም ባለስልጣኑ በሚቆጣጠረው ዘርፍ ላይ እንዲሰማራ የሚሰጠው የንግድ ፈቃድ ነው፡፡

39/ ‹‹**ፈቃድ ያለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ**›› ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ነው፡፡

40/ ‹‹**የምዝገባ መስፈርቶች**›› ማለት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ገበያ በተመለከተ የሚከተሉት ጉዳዮች የሚገዙበት ውስጠ-ደንብ ነው፦

ሀ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመመዝገብ ወይም ለሽያጭ እንዲቀርቡ የመፍቀድ አሰራር፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከምዝገባ ለመሰረዝ ወይም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች፤ ወይም

ለ) በመዝገቡ ውስጥ ስለገቡ አውጪዎች ወይም ሌሎች በመዝገብ እንዲገቡ ስለተፈቀደላቸው ሰዎች አሰራር ወይም ስነምግባር በሚመለከት የሚወጡ ውስጠ-ደንቦች ሆነው፤

1) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የወጡ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው መሠረታዊ ሰነዶች የተካተቱ፤ ወይም

2) በሌላ ሰው ወጥተው በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው በሥራ ላይ የዋሉ፡፡

41/ ‹‹**የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች**›› ማለት ፈቃድ ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የተመዘገቡ ወይም ለሽያጭ የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማለት ነው፡፡

42/ ‹‹**ገበያ ከፋች**›› ማለት ባለስልጣኑ ተግባራዊ በሚያደርገው የቁጥጥር ስርዓት መሠረት ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አቅርቦት እና ፍላጎት እንዲኖር የሚያደርግ ሰው ነው፡፡

43/ ‹‹**ከፍ አድርጎ መዝጋት**›› ማለት ሆን ብሎ የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን የመዝጊያ ዋጋ ከፍ ለማድረግ በማሰብ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በእለቱ የግብይት ማብቂያ የመጨረሻ ሰዓት ላይ ገበያው ላይ ካለው ዋጋ እጅግ ከፍ ባለ ዋጋ መግዛት ነው፡፡

44/ ‹‹**የጋርዮሽ ገንዘብ**›› ማለት ከኢንቨስተሮች ገንዘብን የማሰባሰብ እና የኢንቨስትመንት ስጋቶችን የመጋራት ዓላማ ወይም ውጤት ያለውና ትርፍ እዲከፋፈሉ፣ ወይም ኢንቨስትመንቶቹን ከመግዛት፣ ከመያዝ፣ ከማስተዳደር እና ከማስተላለፍ የሚገኙ ጥቅሞችን በጋርዮሽ ገንዘቡ ለሚሳተፉ ኢንቨስተሮች የሚያስገኙ የባለቤትነት ድርሻዎችን ወይም ክፍልፋዮችን የሚሸጥ ኩባንያ ወይም ሽርክና ማህበር ነው፡፡

45/ ‹‹**ብሔራዊ ባንክ**›› ማለት በተሻሻለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2008 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፡፡

46/ ‹‹**የተውሶ ስም**›› ማለት አንድ ሰው ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤት ጋር ባደረገው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የመጠበቅ ስምምነት መሠረት ሰነዱ በስሙ በገቢና ወጪ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበ ሆኖ የሰነዱ ባለቤትና ተጠቃሚ ሌላ ሰው የሆነበት አሰራር ነው፡፡

47/ ‹‹**ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ**›› ማለት ዕውቅና ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ውጭ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና/ወይም ተዛማጆች በሻጮችና በገዢዎች መካከል በቀጥታ (ፊት ለፊት ወይም እንደ ስልክ እና የኮምፒዩተር መረብ) በሚደረግ ግንኙነት ግብይት የሚደረግበት ገበያ ነው፡፡

48/ ‹‹**የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ**›› ማለት በውክልና ሻጮች አስተባባሪነት አዳዲስ አክሲዮኖችን፣ ቦንዶችን፣ የተስፋ ሰነዶችን፣ እና ሌሎች ገንዘባዊ ሰነዶችን በመሸጥ አዲስ ካፒታል የሚሰበሰብባቸው ገበያ ናቸው፡፡

49/ ‹‹**የመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ**›› ማለት ቁጥጥር በሚደረግባቸዉ ተግባራት ላይ ተቀዳሚ የመቆጣጠር እና በበላይነት የመከታተል ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት አጀንሲ ነው፡፡

50/ ‹‹**ለግል ሽያጭ ማቅረብ**›› ማለት ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ሳያቀርቡ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ኢንቬስተሮች ማቅረብ ነው፡፡

51/ ‹‹**ደንበኛ ሳቢ መግለጫ**›› ማለት በአክሲዮን ኩባንያ ወይም በኩባንያው ስም የወጣ እና ኩባንያው ስላወጣቸው አክሲዮኖች፣ የዕዳ ሰነዶች፣ ወይም ሌሎች የኩባንያው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባህሪ፣ እና ዓላማ የሚገልጹ መረጃዎችን በማካተት ሕዝብ እንዲገዛ ጥሪ የሚደረግበት የጽሁፍ ሰነድ ወይም ሕትመት ነው፡፡

52/ ‹‹**የሕዝብ ኩባንያ**›› ማለት ሰነዶቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ቢመዘገቡም ባይመዘገቡም አክሲዮኖቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የሚሸጡ የአክሲዮን ኩባንያ ነው፡፡

53/ ‹‹**የህዝብ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**›› ማለት በመንግስት ወይም በመንግስት ስም ወይም በመንግስት ተቋማት ስም የሚወጣ ባለዕዳነትን የሚፈጥር ወይም የሚያረጋግጥ ማንኛውም የብድር ስቶክ፣ ቦንድ፣ የተስፋ ሰነድ፣ ወይም ሌላ መሰል ሰነድ ነው፡፡

54/ ‹‹**የመንግስት የልማት ድርጅት**›› ማለት ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ነው፡፡

55/ ‹‹**ለሕዝብ ማቅረብ**›› ማለት አንድ ኩባንያ በንግድ መዝገብ ከመመዝገቡ ወይም አውጪው ኩባንያ ሰነዶቹን ከመሸጡ በፊት ካፒታሉን ለማሰባሰብ በአደራጆቹ አማካኝነት የሚደረግ ሰነዶቹን ለሕዝብ ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ነው፡፡

56/ ‹‹**ለሕዝብ የሚሸጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**›› ማለት በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ላይ የሚሸጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ነው፡፡

57/ ‹‹**ቁጥጥር የሚደረግበት ሰው**›› ማለት በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው እና ባለስልጣኑ የስራ እቅስቃሴውን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ሰው ወይም ፈቃድ የተሰጠው የሰነደ ሙዓለ

ንዋይ ገበያ ወይም ፈቃድ ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ጋር ወይም ከባለፈቃድ ሰው ጋር የሚሰራ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

58/ ‹‹**ውስጠ-ደንቦች**›› ማለት ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ወይም ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ጋር በተያያዘ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ፣ ወይም ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እና የአባላቶቻቸዉ የገበያ እንቅስቃሴ እና የአሰራር ስነ-ምግባር የሚገዙባቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

59/ ‹‹**ሁለተኛ ደረጃ ገበያ**›› ማለት ኢንቬስተሮች በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ በቀጥታ ከአውጪው ወይም ከአገናኙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከሚገዙበት ውጪ አስቀድመው የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከሌሎች ኢንቬስተሮች የሚገዙበት ገበያ ማለት ነው፡፡

60/ ‹‹**ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች**›› ማለት በማንኛውም ሕጋዊ መልክ ያለ በገንዘባዊ ግብይት የድርሻ ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ እና በባለስልጣኑ ፈቃድ መሠረት የሚተላለፍ ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ሀ) በኩባንያ ካፒታል ውስጥ የወጡ ወይም የሚወጡ አክሲዮኖችን፤
- ለ) በኩባንያ የወጡ ወይም የሚወጡ ባለዕዳነትን የሚፈጥሩ ወይም የሚያረጋግጡ ማናቸውም ሰነዶች፤
- ሐ) ብድሮች፣ ቦንዶች፣ እና ሌሎች ወደ ኩባንያ ካፒታልነት ሊቀየሩ የሚችሉ ሰነዶችን፤
- መ) ሁሉም በመንግስት እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የወጡና ለግብይት የሚውሉ የህዝብ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤
- ሠ) ማንኛውም ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር የተያያዘ መብትን፣ ወይም ተዛማጅን፣
- ረ) በጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለ የድርሻ ከፍልፋይን፤
- ሰ) ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል ማንኛውም በባለስልጣኑ ሰነድ ነው ተብሎ የተፈረጀ ወረቀትን ወይም መሳሪያን
  ነገር ግን እንደ ቼክ፣ የተስፋ ሰነድ፣ የሃዋላ ወረቀት፣ የንግድ ወረቀቶችን፣ ሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ ጥሬ ገንዘብ ማስተላለፍ እና በባንኮች መካከል እርስ በርስ ብቻ የሚተላለፉ ሰነዶችን፣ የመድን ፖሊሲዎችን፣ እና ለተጠቃሚዎች ከጡረታ ክፍያዎች የሚመነጩ መብቶችን አያካትትም፡፡

61/ ‹‹**የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ**›› ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማስቀመጥ፣ ክፍያዎችን የማጣራትና የመፈጸም እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን የሚያከናውን ሕጋዊ ድርጅት ነው፡፡

62/ ‹‹**የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ**›› ማለት ፈቃድ ያላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያን የመስሪያ ቦታ በተመለከተ የገበያ መሰረተ-ልማቶችን አካትቶ የሚያቀርብ፣ የሚያዘጋጅ፣ የሚያመቻች ሲሆን በመሠረተ-ልማቱ አማካኝነት፡-

- ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽያጭ፣ ግዥ እና ልውውጥ በቋሚነት የሚደረግበት፤
- ለ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተቀባይነት እንዲያገኙ የታሰቡ ወይም በምክንያታዊነት የሚጠበቁ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመሸጥ፣ ለመግዛት ወይም ለመለዋወጥ የሚደረጉ ጥሪዎች ወይም ግብዣዎች በቋሚነት የሚደረጉበት፤
- ሐ) የተወሰኑ ሰዎች፣ ወይም የተወሰነ መደብ ሰዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመሸጥ፣ ለመግዛት፣ ወይም ለመለዋወጥ ስለሚያቀረቡት ዋጋ ወይም በምክንያታዊነት ያቀርባሉ ተብሎ ስለሚጠበቅበት የሽያጭ ዋጋ፣ ወይም በልዋጭ ስለሚሰጡበት ዋጋ መረጃ በቋሚነት የሚሰጥበት ቦታ፤ ወይም

መ) በገበያው ላይ ግብይት ስለተደረገባቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ክፍያ የመፈጸም ስራ የሚሰራበት፣ ቦታ ነው፡፡

63/ ‹‹**ለማይሸጡ ሰነዶች የግብይት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መፍጠር**›› ማለት ሀብትን ለአንድ ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በውሰት ለመስጠት መዘጋጀት ሲሆን ይህም፡-

ሀ) ለሽያጩ፣ ለማስተላለፉ ወይም ለምደባው ዋጋ የሚከፈለው በባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋሙ ወይም በሌላ ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም በሚወጡ የዕዳ ሰነዶች ወይም የዕዳ ሰነድ ክፍልፋዮች ሲሆን፣ እና

ለ) ለዕዳ ሰነዶቹ ወይም ለዕዳ ሰነድ ክፍልፋዮቹ የሚከፈለው ክፍያ በዋናነት የሚገኘው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሀብቱን ከሚያስገኙት የገንዘብ ፍሰት ሲሆን ነው፡፡

64/ ‹‹**ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት**›› ማለት የራሱን አባላቶች ፍትሃዊና ሀቀኛ እንዲሆኑ እንዲሁም በካፒታል ገበያው ቀልጣፋ አሰራር እንዲሰፍን እና የኢንቬስተሮች እና የህብረተሰቡ ጥቅም እንዲከበር ለማድረግ አባላቱ እንዲከተሉ የሚገባቸውን የስነ-ምግባር ውስጠ-ደንቦች አውጥቶ በአባላቱ ቁጥጥር እንዲያደርግ በዚህ አዋጅ መሠረት እውቅና የተሰጠው ተቋም ነው፡፡

65/ ‹‹**ከፍተኛ ባለሙያ**›› ማለት ለቅጥሩ ወይም ለሹመቱ የባለስልጣኑ ስምምነት ወይም ቅደመ-ይሁንታ የሚያስፈልገው የባለፈቃድ ድርጅት ከፍተኛ የስራ አስፈጻሚ ወይም ሰራተኛ ነው፡፡

66/ ‹‹**አክሲዮን**›› ማለት በአክሲዮን ኩባንያ ላይ ያለ የባለቤትነት ጥቅም ወይም በጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለ የጥቅም ወይም የድርሻ መጠን ነው፡፡

67/ ‹‹**ባለ ልዩ ተልዕኮ ተቋም**›› ማለት፡-

ሀ) ለማንኛቸውም በሃብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለቤቶች ለሆኑ ሰዎች የሚከፈሉ ክፍያዎችን የሚያስገኙ ሀብቶችን እንደ ባለቤት ወይም እንደ አላባ ተጠቃሚ ለመያዝ፣ እና/ወይም

ለ) በሃብት የተደገፈሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለማውጣትና ለመሸጥ

ብቻ የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡

68/ ‹‹**በውክልና ሻጭ**›› ማለት ማንኛውም አውጪው ያወጣቸውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአውጪው ስም ለሽያጭ ለማቅረብ ወይም ለመሸጥ በማሰብ ከአውጪው የሚገዛ ወይም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በውክልና የመሸጥ ተግባር ውስጥ የሚሳተፍ ወይም ተሳትፎ ያለው ሰው ነው፡፡

69/ ‹‹**የዋስትና ሰነድ**›› ማለት ማንኛውም በዋስትና ሰነድ የተደገፈ ቢሆንም ባይሆንም አክሲዮኖችን ወይም የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት መብት የሚሰጥ ሰነድ ነው፡፡

70/ ‹‹**ሰው**›› ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ሰው ማለት ነው፡፡

71/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ ሁሉ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

## 3. የካፒታል ገበያ ባለስልጣን መቋቋም

1/ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን (ከዚህ በኋላ ‹‹ባለስልጣኑ›› እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ ባለስልጣኑ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል፡፡

3/ ባለስልጣኑ የሚከተሉትን ተግባራት ለመፈጸም የሕግ አቅም ይኖረዋል፡-

ሀ) የመክሰስ እና የመከሰስ፤

ለ) የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት የመግዛት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ በይዞታው ስር የማስገባት፣ የማስያዝ፣ ወይም የማስተላለፍ፤

ሐ) ውል የመዋዋል፤ እና

መ) በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራት ለመፈጸም የሚያስፈልጉትንና አንድ ራሱን የቻለ የመንግስት አካል ሊፈጽማቸው የሚችላቸው ሌሎች ማናቸውም ተግባራት የማከናወን፡፡

## 4. ዋና መስሪያ ቤት

የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## 5. የባለስልጣኑ ዓላማ

ባለስልጣኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዓላማዎች ኖሩታል፡-

1/ ኢንቨስተሮችን መጠበቅ ወይም ከለላ መስጠት፤

2/ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማውጣት እና የግብይት ስራ ስርዓት፣ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ግልጽነት በሰፈነበት ሁኔታ የሚካሄድበትን የተሟላ የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳር እዲኖር ማድረግ፤

3/ የካፒታል ገበያው ተኣማኒ እንዲሆኑ በማድረግ መዋቅራዊ የአደጋ ስጋቶችን መቀነስ፤ እና

4/ የረጅም ጊዜ ኢንቬስትመንቶችን የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የካፒታል ገበያን ማስፋፋት፡፡

## 6. የባለስልጣኑ ስልጣን እና ተግባራት

ባለስልጣኑ የተቀመጡለትን ዓላማዎች ለማሳካት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ የተዛማጅ ገበያ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ፣ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ፣ ያልተማከሉ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አገልግሎቶችን ወይም ሌሎች ባለስልጣኑ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቁጥጥር የሚደረግባቸው አገልግሎቶች ናቸው ብሎ የወሰናቸውን ተግባራት ለማከናወን ለሚፈልጉ ሰዎች ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2/ የአገልግሎቱን ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስፈልገውን ወይም ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መከፈል ያለበትን ተመጣጣኝ ዋጋ ተመን ይወስናል፣ ከካፒታል ገበያ ተዋናዮች ላይ ይሰበስባል፡፡

3/ ፈቃድ በተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪዎች ወይም በሌሎች የገበያው ተሳታፊዎች በሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ትስስር እንዲፈጠር የሚያደርግ የመረጃ ቴክኖሎጂ አውታሮችን በማበልጸግ የሚከተሉት ተግባራት ይፈፅማል፡-

ሀ) በተለያዩ አውታሮች ውስጥ እና በአውታሮች መካከል የገበያ መረጃ እንዲተላለፍ እና እንዲሰራጭ በማድረግ ለብዙሀኑ ተጠቃሚዎች መረጃ እንዲዳረስ ያደርጋል፤

ለ) ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች ለሽያጭ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም አገልግሎቶችን በኤሌትሮኒክ መንገድ የሚቀርቡበትን፣ የሚዳረሱበትን ወይም የሚተላለፉበትን መንገድ ያመቻቻል፣ እና

ሐ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግብይቶች የግብይቱ ተሳታፊዎች በአንድ ቦታ በአካል መገናኘት ሳያስፈልጋቸው እንዲፈጸሙ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፡፡

4/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲከስር ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን መከላከያ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የገበያ አገናኞች የገቡባቸውን ግዴታዎች መወጣት ሊሳናቸው የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በመገምገም ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

5/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ሲጣሱ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስዳል፡-

ሀ) የጥፋቶችን ክብደት ወይም ግዝፈት በማመዛዘን የተመጣጣኝነት መርህን መሠረት አድርጎ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚፈጸሙ ጥፋቶች የገንዘብ መቀጮ ይጥላል፤

ለ) በማንኛውም ሰው የተፈጸመ የሕገ-ወጥ ድርጊትን አስተዳደራዊ የምርመራ ውጤት ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠን የንግድ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤ ወይም

መ) በተሠጠው ስልጣን መሠረት በየጊዜው የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ተከትሎ ሌሎች ማናቸውም አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

6/ በስራ ቦታቸው ላይ በመገኘት ወይም ከስራ ቦታቸው ውጭ፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ወይም ሳይሰጥ፡-

ሀ) በሁሉም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች እና ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች ላይ እንዲሁም ማናቸውም አስፈላጊ የሆኑ መዝገቦቻቸው እና ሪኮርዶቻቸው ላይ፤ እና

ለ) በማናቸውም ግብይቶች እና ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች በሚነግዷቸው ወይም ለሕዝብ በሚሸጧቸው ገንዘብ ነክ ሰነዶች ሁሉ ላይ

ቅኝት እና ምርመራ ያደርጋል፡፡

7/ በስራ ቦታ በመገኘት የሚያደርገውን አስተዳደራዊ ምርመራ ወይም ከስራ ቦታ ዉጭ የሚያደርገውን ቅኝት ለማከናወን እነዲረዳዉ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ከራሱ ሰራተኞች በተጨማሪ የፖሊስ ሰራዊትን፣ ዐቃቤ ህግን እና ኦዲተሮችን ሊጠቀም ይችላል፡፡

8/ በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠውን የማንኛውንም ሰው እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን በተፈቀደ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ለሕዝብ ያቀረበ ወይም የተገበያየ ማናቸውንም የሕዝብ ኩባንያ የውስጥ ጉዳይ ይመረምራል ወይም መመሪያ ይሰጣል፡፡

9/ ፈቃድ የተሰጣቸው እና ይሁንታ ያገኙ የገበያ ተዋናዮችን የውጭ ኦዲተር ሹመት ያፀድቃል፡፡

10/ የማናቸውንም ፈቃድ የተሰጣቸው እና ይሁንታ ያገኙ የገበያ ተዋናዮችን ገንዘብ ነክ የስራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ልዩ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ልዩ ምርመራ የሚያደርጉ የውጭ ኦዲተሮችን በኦዲት ተደራጊው የገበያ ተዋናይ ወጪ ቀጥሮ ኦዲት ማስደረግ ይችላል፡፡

11/ የካሳ ፈንድ በአግባቡ እንዲመራ ያመቻቻል፤ እንዲሁም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ የገንዘብ ጉዳት ለሚደርስበት ኢንቬስተር ካሳ ይከፍላል፡፡

12/ ማንኛውም በድርጊቱ ወይም ማድረግ ያለበትን ባለመፈጸሙ ምክንያት ከካሳ ፈንዱ ላይ ገንዘብ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል ያስደረገ ሰው ላይ ክስ ያቀርባል፡፡

13/ ራስን በራስ ለሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፡፡

14/ የገበያ ቅኝት መርሃ ግብር በማዘጋጀት በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ በሚካሄደው ግብይት ላይ ወይም የግብይት ስርዓት ላይ የለት ተለት ቅኝት ማድረግን ጨምሮ ገበያውን በበላይነት በመቆጣጠር፡-

ሀ) የገበያ አገናኞችን አሰራር በቅርበት ይከታተላል፤

ለ) በግብይት ስርዓቱ ላይ በሚደረግ ቅኝት አማካኝነት የተሰበሰበን ማስረጃ ያደራጃል፤ እንዲሁም ይተነትናል፤ እና

ሐ) ከገበያ ተአማኒነት፣ ከገበያ ቅኝት፣ ስጋቶችን በቅርበት ከመከታተል እና ለስጋቶች ምላሽ ከመስጠት አቅም ጋር በተገናኘ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ያለበትን ኃላፊነቶች መወጣቱን ያጣራል፡፡

15/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚያከናውነው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ወይም የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በኤሌትሮኒክ የግብይት መድረኮች የሚካሄድበትን አግባብ ይቆጣጠራል፡፡

16/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች የሚደረጉ ድንበር ዘለል ተግባራትን ለመቆጣጠር እና በገንዘብ ስርዓቱ ላይ መዋቅራዊ አደጋዎች እንዳይከሰቱ ለመከላከል ከሌሎች ተቆጣጣሪ አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል ወይም የጋራ ትብብር ስምምነት ውስጥ ይገባል፡፡

17/ በመጀመሪያ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ገበያዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሽያጭ የሚቀርቡበትንና በኋላም የሚግበያዩበትን ሁኔታ ይቆጣጠራል እንዲሁም ይከታተላል፡፡

18/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መመዝገብ እና ከምዝገባ መሰረዝ በበላይነት ይከታተላል፡፡

19/ በቂ ምክንያት ሲኖር አስተዳደራዊ ምርመራዎችን ያደርጋል፤ እንዲሁም በቁጥጥር ሥራ ሂደት ከማንኛውም በሚመረመረው ጉዳይ ላይ ተሳትፎ ካለው ወይም በሚመረመረው ጉዳይ ላይ መረጃ ሊሰጥ ከሚችል ሰው፣ ቁጥጥር ከሚደረግበት ወይም ከማይደረግበት ሦስተኛ ወገን ተቋም ወይም ግለሰብ ዳታን፣ መረጃን፣ የጽሁፍ ሰነዶችን፣ መዝገቦችን እና ሪኮርዶችን እና በፈቃደኝነት የሚሰጡ የምስክርነት ቃሎችን ይቀበላል፡፡

20/ ይህን አዋጅ በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በፖሊስ እና በዐቃቤ ህግ ውጤታማ የሆነ የምርመራ እና የክስ ሥራ ማከናወን እንዲቻል ከፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እና ከፖሊስ ተቋም ጋር የቅርብ ትብብርና ቅንጅት ይፈጥራል፡፡

21/ በካፒታል ገበያው ላይ በተፈጸሙ የማጭበርበር ድርጊቶች የተገኙ ገቢዎችን ለማስመለስ አዳጋች እንደሚሆን የሚያሰጋ ሁኔታ ለመኖሩ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ባለስልጣኑ ፋይናንስ ተቋማት ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማዘዝ ይችላል፦

   ሀ) የካፒታል ገበያው ተዋናይ ወይም የተዋናዩ ስራ አስፈጻሚ ሂሳብ እንዲታገድ፤

   ለ) በፋይናንስ ተቋሙ ውስጥ ባለ በጥንቃቄ የሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ የተቀመጠ ማንኛውም የካፒታል ገበያ ተዋናዩ ጥሬ ገንዘብ፣ውድ እቃ፣የከበረ ጌጣጌጥ፣ ወይም ሌላ ንብረት እንዳይንቀሳቀስ፤ እና

   ሐ) በጥንቃቄ በሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ ስለሚገኙ ሀብቶች ተገቢውን መረጃ ለባለሥልጣኑ እንዲሰጥ፡፡

22/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 21 መሰረት ባለስልጣኑ ለፋይናንስ ተቋሙ የማገጃ ትዕዛዝ በደረሰው በ10 (አስር) ቀናት ጊዜ ውስጥ እገዳው እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማግኘት አለበት፡፡

23/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 22 ላይ በተመለከተው አግባብ የእግድ ትእዛዝ ከፍርድ ቤት ካልመጣ እገዳው እንደጸና እግድ አይቆጠርም፡፡

24/ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ለሕዝብ ወይም ለተወሰነ የሕበረተሰብ ክፍል ያቀረበን ኩባንያ መልካም አስተዳደር በተመለከተ ማስታወቂያዎችን እና የአሰራር መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

25/ ግልጽ፣ ሚዛናዊ፣ ፍትሃዊ እና ወጥነት ያላቸውን የአሰራር ሥርዓት አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

26/ የኢንቬስተሮችን ስልጠና እና ንቃት ያሳድጋል፡፡

27/ ለአንቬስተሮች ተገቢውን ጥበቃ ለማድረግ የገበያውን ፍትሃዊነት፣ዉጤታማነት እና ግልጽነት ለማረጋገጥ እና ሌሎች የገበያ ስጋቶችን ለማስወገድ እንዲያስችለው ሰነዶችን፣ ገበያዎችን፣ የገበያ ተዋናዮችን እና ተግባሮቻቸውን በየጊዜው ይገመግማል፡፡

28/ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች መካከል የሚፈጠርን የጥቅም ግጭት እና በማትጊያ ክፍያዎችና በሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል የሚከሰትን ያለመጣጣም ይለያል፣ ይከላከላል፣ ያስወግዳል፣ ይፋ ያደርጋል፣ ወይም ይቆጣጠራል፡፡

29/ ተለዋዋጭ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን፣ እየተፈጠሩ ያሉ አዳዲስ ስጋቶችን፣ እንዲሁም የቁጥጥር ስርዓቱን መሻሻል አስፈላጊነትን ለመዳሰስና ለመለየት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የቁጥጥር ወሰን በየጊዜው ይገመግማል፡፡

30/ ዓላማዉን ለማሳካት እና ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

## 7. <u>የባለስልጣኑ አቋም</u>

ባለስልጣኑ፡-

1/ የዳይሬክተሮች ቦርድ (ከዚህ በኋላ ‹‹ቦርዱ›› እየተባለ የሚጠራ)፣

2/ ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እንዲሁም

3/ አስፈላጊ ሰራተኞች

ይኖሩታል፡፡

## 8. <u>የቦርደ አባላት ስብጥር እና አመዳደብ</u>

1/ ቦርዱ ከሚከተሉት አካላት የተውጣጣ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ— ቋሚ አባል፤
   ለ) የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ዋና ዳይሬክተር— ቋሚ አባል፤
   ሐ) ሌሎች በዘርፉ ሙያዊ ብቃት ያላቸው አራት ሰዎች— አባል፤ እና
   መ) የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር— ያለ ድምፅ የሚሳተፍ አባል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተጠቀሱት የቦርድ አባላት የሚሾሙት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

3/ የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቶቹ መካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማል፤ ሆኖም ግን ዋና ዳይሬክተሩ የቦርዱ ሰብሳቢ መሆን አይችልም፡፡

4/ የቦርዱ ሰብሳቢ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተጠቀሱት የቦርድ አባላት የሚመረጡት በሕግ፣ በፋይናንስ፣ በምጣኔ ሀብት፣ በስራ አመራር እና ተያያዥ የሙያ ዘርፎች ልምድና የሙያ ብቃት ካላቸው ሰዎች መካከል ይሆናል፡፡

5/ ቦርዱ ዋና ዳይሬክተሩ የማይገባበትና ቢያንስ ሦስት አባላቱን ያካተተ የኦዲት ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

6/ ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ኮሚቴዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

7/ የቦርድ አባላቱ የስራ ዋጋ እና አበል መንግስት በሚወስነው መሠረት ከባለስልጣኑ ጠቅላላ ፈንድ ላይ የሚከፈል ይሆናል፡፡

## 9. የጥቅም ግጭት

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተጠቀሱት የቦርድ አባላት የጥቅም ግጭት ውስጥ የሚያስገቧቸውን ሌሎች ኃላፊነቶች ሊቀበሉ አይችሉም፡፡

2/ የቦርድ አባላት የጥቅም ግጭት ውስጥ በሚያስገቧቸው ጉዳዮች ላይ ድምጽ ከመስጠት ራሳቸውን በራሳቸው ማግለል አለባቸው፡፡

## 10. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን

1/ የቦርዱ ሰብሳቢ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተጠቀሱት የቦርድ አባላት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የቦርዱ አባላት የአገልግሎት የስራ ዘመን ለሌላ አምስት ዓመት ሊራዘም ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ቢኖርም፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) መሠረት ከሚሰየሙ የመጀመሪያው ዙር ቦርድ አባላት መካከል የሁለቱ አባላት የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሰረት የስራ ዘመናቸው ስድስት ዓመት የሚሆነው የቦርድ አባላት እነማን እንደሆኑ ለሹመት በሚቀርቡበት ጊዜ ይወሰናል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የሥራ ዘመናቸው ስድስት ዓመት የሆኑ የቦርዱ አባላት የአገልግሎት ዘመናቸው ሊራዘም አይችልም፡፡

## 11. የቦርዱ አባላት ከሀላፊነት ስለመነሳት ወይም ስለመልቀቅ

1/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) መሠረት የተሾመ የቦርድ አባል ከሀላፊነቱ የሚነሳው ወይም የሚለቀው፡-

ሀ) ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የመልቀቂያ ጥያቄ ሲያቀርብ እና የመልቀቂያ ጥያቄው ተቀባይነት ሲያገኝ፤

ለ) በአእምሮ ሕመም ወይም በአካል ሕመም ምክንያት የመስራት አቅም ሲያጣ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ኃላፊነቱን ለመወጣት የማይችል ወይም የማይበቃ ሲሆን ወይም በአባልነት መቀጠል የማይችል ከሆነ፤

ሐ) ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም በቂ ምክንያት ሳይኖረው ከሦስት በላይ በሆኑ ተከታታይ የቦርዱ ስብሰባዎች ሳይገኝ ከቀረ፤

መ) የመክሰር ውሳኔ የተወሰነበት ከሆነ ወይም ከባለገንዘቦቹ ጋር የመጠባበቂያ ስምምነት ውስጥ ከገባ፣

ሠ) ስድስት ወር ወይም ከዚያ የሚበልጥ የእስር ውሳኔ በፍርድ ቤት የተላለፈበት ከሆነ፤ ወይም

ረ) ከእምነት ማጉደል፣ ከማታለል ወይም ከስነምግባር ንቅዘት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠበት

ነዉ፡፡

2/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) መሠረት የተሾመ የቦርድ አባል የስራ ዘመኑን ሳያጠናቅቅ ከኃላፊነቱ የተነሳ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተሰናባቹ የቦርድ አባል ሳያጠናቅቅ የቀረውን የስራ ዘመን የሚያጠናቀቅ ተተኪ የቦርድ አባል ይሾማል፡፡

3/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) መሠረት የተሾመ የቦርድ አባል ለተወሰነ ጊዜ ኃላፊነቱን መወጣት የማይችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አባሉ ለማይኖርበት ለተወሰነው ጊዜ ሌላ የቦርድ አባል ይሾማል፡፡

## 12 . የቦርዱ ስልጣን እና ተግባራት

1/ ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት አሉት፡-

ሀ) በባለስልጣኑ የሚወጡ መመሪያዎችን ማጽደቅ፤

ለ) የባለስልጣኑን በጀት ማጽደቅ፤

ሐ) የባለስልጣኑን እስትራቴጅያዊ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የስራ መርሐ-ግብሮችን እና የስራ አፈጻጸም ሪፖርት መገምገም፤

መ) በዋና ዳይሬክተሩ በሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብ መሠረት የባለስልጣኑን የሰራተኞች የደሞዝ እና የጥቅማጥቅም መዋቅር ማጽደቅ፤

ሠ) የባለስልጣኑን ስልጣንና ተግባር በበላይነት መምራት፤

ረ) የባለስልጣኑን ሂሳቦች የሚመረምሩ የዉጭ ኦዲተሮችን መሾም፤ እና

ሸ) ባለስልጣኑ በውክልና ለሌሎች የሚሰጣቸውን ስልጣኖች እና ኃላፊነቶች ማጽደቅ፡፡

2/ የቦርዱ ኦዲት ኮሚቴ የውስጥ እና የውጭ ኦዲተሮች የሚያቀርቡትን ሪፖርቶች ግኝቶች እና የውሳኔ ሀሳቦች ተቀብሎ ይመረምራል፤ እንዲሁም ለአፈጻጸሙም አስፈላጊ ትዕዛዞችን ይሰጣል፡፡

## 13. የቦርዱ የስብሰባ ስነ-ሥርዓት

1/ ከቦርዱ አባላት አራቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሟላል፡፡

2/ ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ይሁን እንጂ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ሰብሳቢው ከሌለ እሱ የወከለው ሰው በማንኛውም ጊዜ ወይም ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ከአባላቱ ሦስቱ ስብሰባ እንዲደረግ ከጠየቁ አስቸኳይ የቦርድ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

3/ ሁሉንም የቦርድ ስብሰበዎች የሚመራው ሰብሳቢው ወይም በሰብሳቢው የተወከለ ሰው ይሆናል፡፡

4/ ሁሉም የቦርድ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው በተገኙት አባላት ተራ የድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

5/ ቦርዱ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

6/ የቦርዱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች በትክክል መመዝገብና አያያዛቸው እና አጠባበቃቸው ቦርዱ በሚወስነው ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡

7/ ቦርዱ ካልወሰነ በቀር የቦርድ ቃለ ጉባኤዎች ሚስጢራዊነት የተጠበቀ ይሆናል፡፡

8 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 14. የዋና ዳይሬክተር ሹመት፣ ስልጣን እና ተግባራት

1/ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የሚሾመው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡፡

2/ በዋና ዳይሬክተርነት የሚሾም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟላ ይገባል፡-
  ሀ) በፋይናንስ፣ በምጣኔ ሀብት፣ በስራ አመራር፣ በሕግ እና ተዛማጅ የሙያ ዘርፎች በከፍተኛ የስራ አመራር ደረጃ ቢያንስ የአስር ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤ እና
  ለ) በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ወይም በካፒታል ገበያ ወይም በፋይናንስ ልዩ ብቃት ያለው፡፡

3/ ዋና ዳይሬክተሩ ከምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ዉጭ ሌሎች ከፍተኛ የስራ አስፈጻሚዎችን በማጨት ቦርዱ ሹመታቸውን እንዲያጸድቅ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

4/ ዋና ዳይሬክተሩ በአዋጁ መሠረት እና ቦርዱ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች መሰረት የባለስልጣኑን አስተዳደር እና የስራ ሂደት በበላይነት ይከታተላል፤ ይመራል፡፡

5/ ዋና ዳይሬክተሩ የበለስልጣኑን የስራ ዕቅድና የዓመት በጀት ያዘጋጃል፤ በቦርዱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

6/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለስልጣኑ ዋና ተወካይ/እንደራሴ ነው፤ በእንደራሴነት ስልጣኑም ቀጥለው የተመለከቱትን ያከናውናል፡-

ሀ) ባለስልጣኑ ከሌሎች ሰዎች፣ ከመንግስት፣ እና አባል ከሆነባቸው ዓለም-አቀፍ ተቋማት ጋር በሚያደርጋቸው ማንኛውም ግንኙነቶች ባለስልጣኑን ይወክላል፤

ለ) ብቻውን ወይም ከሌሎች ኃላፊነት ከተሰጣቸው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ጋር በጣምራ ባለስልጣኑ በሚገባባቸው ውሎች፣ በወቅታዊ ሪፖርቶች፣ በሂሳብ ሚዛን፣ በትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ፣ በደብዳቤ ልውውጦች እና በሌሎች የባለስልጣኑ ሰነዶች ላይ ይፈርማል፤

ሐ) ባለስልጣኑ በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ወቅት ሁሉ ራሱ ወይም በነገረ ፈጅ አማካኝነት የባለስልጣኑ ወኪል ይሆናል፤ እና

መ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የባለስልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡፡

7/ የባለስልጣኑን የለት ተለት ስራ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ዋና ዳይሬክተሩ ካለው ስልጣንና ኃላፊነት ላይ እንዳስፈላጊነቱ በከፊል ለምክትሎቹ ወይም ለሌሎች ሰራተኞች በውክልና ሊሠጥ ይችላል፡፡

## 15. ምክትል ዋና ዳይሬክተር

1/ የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ ዋና ዳይሬክተር ሆኖ ማገለገል የሚያስችል ብቃት ያላቸው ሆነዉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ይሆናሉ፡፡

2/ የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ዋና ዳደሬክተሩን ያግዛሉ፤ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ የዋና ዳይሬክተሩን ስራዎች ያከናውናሉ፡፡ የተቋሙን ስራዎች በማቀድ፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፣ በዘርፍ ተለይቶ የሚሰጡዋቸውን የስራ ክፍሎች ይመራሉ፡፡

## 16. ስልጣን እና ተግባራት በውክልና ስለመስጠት

1/ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ማንኛውንም ስልጣን እና ተግባራት፡-

ሀ) ለአንድ የተለየ ተልዕኮ ለተቋቋመ ኮሚቴ፤

ለ) እውቅና ለተሰጠው ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት፤ ወይም

ሐ) ለግለሰቦች

በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2/ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ማንኛውንም ተግባርና ኃላፊነት ውክልና በሚሰጥበት ጊዜ፣ ውክልና የተሰጠው አካል ማከናወን ስለሚችላቸው ተግባርና ሀላፊነቶች በግልፅ ለይቶ ማስቀመጥ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሰጠ ውክልና መመሪያ ለማውጣት አይሰራም፡፡

4/ ባለስልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የሰጠውን የውክልና ስልጣን ለመሻር ይችላል፡፡

## 17. ለባለስልጣኑ መረጃ ስለመስጠት

1/ ባለስልጣኑ ወይም በባለስልጣኑ የተወከለ ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ የቁጥጥር ስልጣን ውስጥ በሚካተቱ የስራ ዘርፎች ላይ የተሰማራን ማንኛውም ሰው በጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት በማስታወቂያው በተጠቀሰው አግባብና ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ ለወከለው ሰው መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ የባለስልጣኑን ዓላማ ለማሳካት ካልሆነ በቀር ወይም በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በቀር ባለስልጣኑ ወይም ማንኛውም የባለስልጣኑ ሰራተኛ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተገኘን ማንኛውንም መረጃ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት አይችልም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተገለጸው ቢኖርም ባለስልጣኑ ጥያቄ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት ለሌሎች በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ ተቆጣጣሪ ተቋማት የሕግ ወይም የቁጥጥር ደንብ ጥሰት የፈጸመ ወይም እየፈጸመ ያለን ሰው ለይተው ሲያመለክቱ ያንን በተመለከተ የሚያደርጉትን አስተዳደራዊ ምርመራ ለማገዝ መረጃን ሊያጋራ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገዉ የመረጃ ማጋራት ተፈፃሚ የሚሆነው፡-

- ሀ) ባለስልጣኑ ከመረጃ ጠያቂዉ የውጭ አቻ ተቋም ጋር የመረጃ ልውውጥ ስምምነት ካለዉ ወይም ኢትዮጵያ የገባችበት የዓለም አቀፍ ስምምነት ካለ፤ እና
- ለ) ምርመራው የሚደረግበት ጉዳይ ጠያቂው የውጭ ተቆጣጣሪ ተቋም የሚያስፈጽመው ወይም የሚያስተዳድረው ጉዳይ ከሆነ፤ ወይም በጠያቂው ተቋም የስልጣን ወሰን ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ

ብቻ ነው፡፡

5/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) አፈጻጸም ዓላማ በንዑስ አንቀጹ የተጠቀሰው የሕግ ወይም የቁጥጥር ደንብ ጥሰት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተፈጸመ የሕግ ጥሰት ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች አስፈላጊው ለውጥ ተደርጎባቸው ተፈጻሚ ይደረጋሉ፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት እገዛ የሚጠይቅ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፡-

ሀ) የተጠየቀው እገዛ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አስፈላጊ መሆኑን፤ ወይም

ለ) የተጠየቀው እገዛ የጠያቂውን ባለስልጣን ተግባራቱን እና ግዴታዎቹን ለመወጣት እንደሚጠቅመው

ማሳየት አለበት፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ላይ የተገለጸው ቢኖርም፣ ባለስልጣኑ ለተጠየቀው እገዛ ውሳኔ ለመስጠት፡-

ሀ) እገዛውን ለማድረግ ያወጣውን ወጪ እገዛ ጠያቂው ባለስልጣን መሸፈን አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን፣ እና

ለ) ከኢትዮጵያ ተመሳሳይ የእገዛ ጥያቄ ቢቀርብለት በተራው እገዛ ለማድረግ የሚፈቅድ እና አቅም ያለው መሆን አለመሆኑን

ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

8/ የሚደረገው ትብብር ወይም የሚፈጸመው ቅንጅት በዚህ አዋጅ ከተመለከቱት ዓላማዎቹ ጋር የሚጻረር እስካልሆነ ድረስ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ማንኛውም ድንጋጌ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ስልጣን ተግባራዊ ለማድረግ ከሌላ ማናቸውም ተቆጣጣሪ ተቋማት ጋር ከመተባበር ወይም ስራውን ከማቀናጀት ሊከለክለው አይችልም፡፡

9/ የባለስልጣኑ ሰራተኞች የጥቅም ግጭትን መለየት፣ መከላከል ወይም ማሳወቅ እንዲሁም ፍትሃዊ የስነ-ስርዓት ደንቦችን መከተል አለባቸው፡፡

## 18. የባለስልጣኑ የገንዘብ ምንጮች

1/ የባለስልጣኑ የገንዘብ ምንጭ፡-

ሀ) ባለስልጣኑ ከሚሰጣቸው ፈቃዶች እና በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ጋር በተያያዘ ከሚከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎች፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚጣሉ አስተዳዳራዊ መቀጮዎች ጋር በተያያዘ ከሚሰበሰቡ ገንዘቦች፤ እና

ሐ) ሌሎች በድጋፍ ከሚገኙ ገንዘቦች

የተውጣጣ ይሆናል፡፡

2/ በአጭር ጊዜ ውስጥ የማይፈለጉ ገንዘቦችን ባለስልጣኑ በሚወስነው መሠረት በኢንቬስትመንት ላይ ያውላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የባለስልጣኑ የገንዘብ ምንጮች የባለስልጣኑን ወጪዎች ለመሸፈን የማይበቃ በሚሆንበት ጊዜ ጉድለቱ በመንግስት ከሚመደብ በጀት ይሸፈናል፡፡

## 19. የባለስልጣኑ ሂሳቦች

1/ ባለስለጣኑ ስራዎቹ፣ ገንዘቦቹ እና ንብረቶቹ በአግባቡ ለመጠበቃቸው ተገቢ የሂሳብ መዝገቦች እና ሌሎች ሪኮርዶች መያዛቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2/ የበጀት ዓመቱ ካበቃ በኋላ ባሉት 3 (ሶስት) ወራት ውስጥ ባለስልጣኑ የሂሳብ ሪፖርት እና ሌሎች የስራ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት አለበት፡፡

3/ የባለስልጣኑ የሂሳብ ሪፖርቶች አዘገጃጀት ዓለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት መንገድን የተከተለ ወይም የሚመለከተው የመንግስት ባለስልጣን የሚያወጣውን ሌላ የሂሳብ አዘገጃጀት ስርዓት የተከተለ መሆን አለበት፡፡

## 20. <u>የባለስልጣኑን ሂሳቦች በውጭ ኦዲት ስለማስመርመር</u>

1/ የባለስልጣኑ ሂሳቦች በየዓመቱ በውጭ ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

2/ የፋይናንስ ዓመቱ ካበቃ በኋላ ባሉት 3 (ሶስት) ወራት ውስጥ የኦዲት ሪፖርቱ ተጠናቆ ቦርዱ እንዲመረምረው እና እንዲያጸድቀው ለቦርዱ የኦዲት ኮሚቴ መቅረብ አለበት፡፡

3/ በውጭ ኦዲተር በአግባቡ ተመርምሮ የተፈረመው የኦዲት ሪፖርት ባለስልጣኑ በሚያሳትመው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ መካተት አለበት፡፡

## 21. <u>የባለስልጣኑ የበጀት ዓመት</u>

የባለስልጣኑ የበጀት ዓመት በየዓመቱ እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 ጀምሮ ያለው ተከታታይ የአስራ ሁለት ወራት ክፍለ ጊዜ ነው፡፡

# ክፍል ሶስት
# ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እውቅና ስለሚያገኝበት ሁኔታ

## 22. <u>እውቅና ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1/ በካፒታል ገበያ ባለስልጣን የቁጥጥር ስልጣን ስር የሚንቀሳቀስ እና እንደ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ዕውቅና ተሰጥቶት መስራት የሚፈልግ ተቋም በተዘጋጀው የማመልከቻ ፎርም መሠረት ለባለስልጣኑ ማመልከት አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም በባለስልጣኑ እውቅና የተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልገው ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚቀርብ ማመልከቻ አመልካቹ ዕውቅና ከተሰጠው በኋላ ስለሚያከናዉናቸዉ ሥልጣንና ተግባራት መጥቀስ አለበት፡፡

2/ ባለስልጣኑ ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት እውቅና የሚሰጠው አመልካቹ ድርጅት፡-

ሀ) ከዚህ አዋጅ፣ እና ተያያዥነት ካላቸው ደንቦችና መመሪያዎች ጋር የተጣጣመ ውስጠ-ደንቦችና ፖሊሲዎች ያሉት መሆኑን፣

ለ) የሕግና እና ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸው መመሪያዎች ጥሰት መቆጣጠርን ጨምሮ የተጣለበትን ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚያስችል የገንዘብ አቅም እና የአስተዳደራዊ ብቃት ያለው መሆኑን፤

ሐ) ብቁ እና ተገቢ መሆኑን፤

መ) ስራውን ለማከናወን የሚችሉ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ያሉት መሆኑን፤ እና

ሠ) ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚወስናቸውን ሌሎች መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን

ያረጋገጠ ከሆነ ነው፡፡

5/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የቀረበን ማመልከቻ በተመለከተ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን የውለታ ቃሎችን እና ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ አመልካቹ አካል እውቅና የተሰጠው ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት መሆኑን ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ለሕዝብ ያስታውቃል፡፡

## 23. ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት በውክልና የሚሰጥ ሥልጣን እና ተግባራት ማካተት ስላለባቸው ሁኔታዎች

ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት የሚሰጥ የሥልጣን እና ተግባራት ውክልና ከዚህ ቀጥለው የተመለከቱትን ማካተት አለበት፡-

1/ ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት በውክልና የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር፤

2/ የዲሲፕሊን እርምጃች እንዲወስድ የተሰጠው የስልጣን ውክልና እና ሊወስዳቸው የሚችላቸው አስተዳደራዊ የቅጣት ወሰን እስከምን ድረስ እንደሆነ፤

3/ በውክልና የተሰጠው ስልጣን ወይም ተግባር ስለሚፈጸምበት ሁኔታ የሚያመለክቱ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች፤

4/ ራሱን በራሱ በሚቆጣጠር ድርጅት ስም በውክልና የተሰጠውን ስልጣን ወይም ተግባር እንዲያስፈጽሙ የተወከሉ ግለሰቦች፤

5/ በውክልና የተሰጠውን ስልጣን ወይም ተግባር አፈጻጸም በተመለከተ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ለባለስልጣኑ በየወቅቱ ሪፖርቶችን ስለሚያቀርብበት አግባብ፤ እና

6/ ባለስልጣኑ በውክልናው ላይ የሚያመለክተው ማንኛውም ሌላ ጉዳይ፡፡

## 24. የራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ውስጠ-ደንቦች

1/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በውክልና ከተሰጠው ተግባር ጋር በተያያዘ የሚጣሉ ማናቸውም ቅጣቶችን እና የሚሠራባቸውን የዲሲፒሊን ስልጣኖቹን ጨምሮ ከቁጥጥርና በበላይነት ክትትል የማድረግ ሥራው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ውስጠ-ደንቦችን ያወጣል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡት ውስጠ-ደንቦች ቀጥለው የተመለከቱን ጉዳዮች ማመልከት አለባቸው፡-

ሀ) የአባላቱን፣ የኢንቬስተሮችን እና የአገልግሎታቸው ተጠቃሚዎችን ጥቅም፣ መብትና ተጠያቂነትን ታሳቢ ያደረገ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት አስተዳደራዊ መዋቅርን እና የባለ አክሲዮኖች መብቶችን፤

ለ) የአባልነት ውስጠ-ደንቦች እና የአባልነት ጥያቄ ስለሚጸድቅበት እና አባል ስለሚቀበልበት ቅድመ ሁኔታዎች፤

ሐ) ሁሉም አባላት የሚስተናገዱበት ፍትሃዊ እና ወጥነት ያለው አሰራር እና በዳይሬክተሮች አመራረጥ እና በአስተዳደሩ አባላት ስለሚኖራቸው ፍትሃዊ ውክልና፤

መ) በአባላት፣ በተጠቃሚዎች፣ በኢንቬስተሮች እና በደንበኞቻቸው መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት መንገድ እና ለባለስለጣኑ ወይም ለሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ ይግባኝ ለማቅረብ ስለሚኖራቸው መብት፤

ሠ) ሊፈጠሩ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶች ስለሚፈቱበት መንገድ እና ከባለስልጣኑ ጋር የህግና ደንብ ጥሰቶችን ስለመመርመር እንዲሁም ሕግና ደንብን ለማስፈጸም ስለሚደረግ ትብብር፤

ረ) ከባለስልጣኑ ውጭ ላለ ለማንኛውም የመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ ስለሚኖር ተጠያቂነት እና ስለ ሪፖርት አቀራረብ የሚደነግግ ውስጠ-ደንቦች እና ስነ-ስርዓቶች፤

ሰ) በባለስልጣኑ በተቀመጠው የመረጃ ጥበቃ መርሆች መሠረት የመረጃ ባለቤቶች መረጃ ስለሚጠበቅበት መንገድ፤

ሸ) ጸረ-ውድድር አሰራሮችን ስለማስቀረት፤

ቀ) ስለ አባላቱ ስነ-ምግባር፤ እና

በ) ስለ ኢንቬስተሮች ጥበቃ እና ስለ ገበያው ተአማኒነት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚዘጋጅ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ውስጠ-ደንብ ለባለስልጣኑ ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት ተግባራዊ መሆን የለበትም፡፡

4/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት በመመስረቻ ደንቡ ላይ የሚያደርጋቸውን ማንኛውም ማሻሻያዎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት ለባለስልጣኑ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት፡፡

## 25. <u>ውሳኔ ላይ ስለሚደረግ ገደብ</u>

ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት፡-

1/ መብቱ የሚነካበት ሰው በጉዳዩ ላይ የራሱን አስተያየት እንዲያቀርብ ዕድል ካልሰጠ፤ ወይም

2/ የውሳኔው መዘግየት የሸማቾች መብትን አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን ምክንያታዊነትን መሠረት አድርጎ ካልገመተ፤

በስተቀር በራሱ ውስጠ-ደንቦች መሠረት የአንድን ሰው መብት የሚጎዳ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም፡፡

## 26. የዲሲፕሊን እርምጃ

1/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የውስጠ-ደንቦቹን ድንጋጌ በሚጥስ በማንኛውም አባሉ ላይ ራሱ በሚያወጣው ውስጠ-ደንብ መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት የሚወስደው የዲሲፕሊን እርምጃ ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃድ የሰጠውን ሰው በተመለከተ ተጨማሪ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣኑን አይገድብም፡፡

3/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወስድ በሁለት ቀናት ውስጥ የአባሉን ስም፣ የተወሰደውን እርምጃ ምክንያት፣ የተጣለውን የገንዘብ መቀጮ መጠን እና የእገዳ እርምጃ ተወስዶ ከሆነ እገዳው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በተወሰነው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ያመለከተ እንደሆነ ባለስልጣኑ ቅሬታ ላቀረበው ሰውና ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት የመሰማት መብት ከሰጠ በኋላ ውሳኔውን በድጋሚ በመመርመር ሊያጸናው፣ ሊለውጠው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም እንኳን ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት አባሉ ላይ እርምጃ ሳይወስድ የቀረ እንደሆነ ባለስልጣኑ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠርን ድርጅት አባል ከማገድ፣ ከአባልነቱ ከማስወገድ ወይም ሌሎች የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ከመውሰድ ሊያግደው አይችልም፡፡

6/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት ፈቃድ የተሰጠውን ሰው እና ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት በጉዳዩ ላይ የመሰማት መብት ይጠብቅላቸዋል፡፡

7/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተመለከቱትን ማናቸውንም ጉዳዮች አስመልክቶ ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት ተገቢውን የመሰማት ዕድል እንዲያገኝ ካደረገ በኋላ በጽሁፍ ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጠው ይችላል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) መሰረት የሚሰጥ ትዕዛዝ፡-

ሀ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት መተዳደሪያ ሰነድ ወይም ውስጠ-ደንቦች በሚሰጠው ትእዛዝ ወይም መመሪያ ለተመለከተው ጊዜ እንዳይሰራበት ለማገድ፤

ለ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት ሰነዱን ወይም ውስጠ-ደንቦቹን እንዲያሻሽል ማድረግ፤ ወይም

ሐ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት መተዳደሪያ ሰነዱን ወይም ውስጠ-ደንቦቹን እንዲያስፈጽም ወይም እንዲተገብር ማድረግ፤

ሊሆን ይችላል፡፡

## 27. የከፍተኛ ባለሙያ ሹመት እና ለውጥ

1/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ለማድረግ ያሰበውን የከፍተኛ ባለሙያ ሹመት ወይም ለውጥ አስቀድሞ በጽሁፍ ለባለስልጣኑ ሳያሳውቅ ከፍተኛ ባለሙያ ሊሾም ወይም ለውጥ ሊያደርግ አይችልም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ማሳወቂያ ሲሰጠው ባለስልጣኑ ተቃውሞውን በ15 ቀናት ውስጥ ያልገለጸ እንደሆነ የከፍተኛ ባለሙያው ሹመት ወይም ለውጥ የጸና ይሆናል፡፡

## 28. ከፍተኛ ባለሙያን ስለማንሳት

ባለስልጣኑ በበቂ ምክንያት፡-

1/ የራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ከፍተኛ ባለሙያ ድርጅቱን ለመምራት ብቃት እና ተገቢነት የለውም ብሎ ሲያምን፤ ወይም

2/ የከፍተኛ ባለሙያው መሾም ወይም በሹመቱ መቀጠል ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት አደጋ ላይ ይጥላል የሚል እምነት ካለው ወይም የኢንቬስተሮችን እና የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ጥቅም ይጎዳል ወይም የአንድ የተለየ ዘርፍ ወይም ኢንዱስትሪ አባላትን ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን

ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠረው ድርጅት እና ለከፍተኛ ባለሙያው የመሰማት ዕድል ከሰጣቸው በኋላ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረውን ድርጅት ከፍተኛ ባለሙያውን እንዳይሾመው ወይም ከኃላፊነት እንዲያነሳው ለማዘዝ ይችላል፡፡

## 29. ዓመታዊ ሪፖርት

1/ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እያንዳንዱ የበጀት ዓመት ካበቃ በኋላ ባሉት አራት ወራት ውስጥ ለባለስልጣኑ የዓመቱን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ሪፖርት የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ መሆን አለበት፡-

ሀ) ራሱን በራሱ ስለሚቆጣጠር ድርጅት መልካም አስተዳደር ፖሊሲ እና አፈጻጸም ሪፖርትን፤

ለ) ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት የሂሳብ መግለጫቸውን እንዲያዘጋጁ በሚገደዱበት አኳሃን የተዘጋጀ የሂሳብ መግለጫን፤

ሐ) ሌላ በባለስልጣኑ መመሪያ የተቀመጡ አስፈላጊ መረጃዎችን፡፡

3/ የውጭ ኦዲተር በምርመራው ወቅት የሚከተሉትን ጥፋቶች ለመኖራቸው በቂ ምክንያት ኖሮት የጠረጠረ ከሆነ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) ራሱን በራሱ ከሚቆጣጠር ድርጅት ስራ ጋር በተያያዘ የስጋቶች ደረጃ በአሳሳቢ መልኩ ስለመቀየሩ ወይም ተቀይሮ እንደነበር እና ይህም የድርጅቱን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን፤

ለ) ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ማንኛውንም የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም ባለስልጣኑ የሰጠውን ትዕዛዝ ጥሶ ሊሆን እንደሚችል፤

ሐ) የፋይናንስ ወንጀል ተፈጽሞ ከሆነ ወይም ሊፈጸም የሚችል ከሆነ፤ ወይም

መ) ከፍተኛ የአሰራር መዛባት ተከስቶ ከሆነ፡፡

4/ ኦዲተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ሪፖርት ማቅረቡ የኦዲተርን ግዴታ እንደጣሰ ሊቆጠርበት አይችልም፡፡

# ክፍል አራት
# የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ

## 30. ሕገ ወጥ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ስለመከልከል

1/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ፈቃዱ በባለስልጣኑ ሳይፀድቅለት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ወይም የተዛማጅ ውሎች ገበያን ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አገልግሎት ለማቋቋምና ለመስራት ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም የተዛማጅ ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አገልግሎት ለመክፈት ወይም ለመጀመር አይችልም፡፡

2/ ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ‹‹የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ›› ወይም ‹‹የተዛማጅ ውሎች ገበያ›› የሚሉ ቃላቶችን ከንግድ ስራው ጋር በተያያዘ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

## 31. የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን ስለመመስረት

1/ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ (ከዚህ በኋላ ‹‹ገበያው›› እየተባለ የሚጠራ) በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ፣ የውጭ ኢንቬስተሮችን ጨምሮ፣ ትብብር በአክሲዮን ኩባንያ መልክ ይቋቋማል፡፡

2/ የመንግስትና በመንግስት የተያዙ ድርጅቶች ከገበያው ካፒታል ላይ የሚኖራቸው ድርሻ ከ25 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው ቢኖርም ከግሉ ዘርፍ የገበያውን ካፒታል ድርሻ ለመያዝ በቂ ፍላጎት ከሌለ መንግስት ገበያውን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ያህል ተጨማሪ ካፒታል ለመያዝ ይችላል፡፡

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተገለጸው ቢኖርም ከግሉ ዘርፍ፤ የውጭ ኢንቬስተሮችን ጨምሮ፤ የገበያውን ካፒታል ድርሻ ለመያዝ ምንም ፍላጎት ከሌለ ገበያው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ ይቋቋማል፡፡

5/ ባለስልጣኑ ገበያው የአነስተኛ የካፒታል መመዘኛ፣ የተገቢነት እና ብቁነት መስፈርት፣ የስራ እና ስራ አመራር ሁኔታን፣ የብቃት ማስረጃ፣ እና ሌሎች ባለስልጣኑ በመመሪያ የሚደነግጋቸው ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ የገበያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

6/ በዚህ አንቀፅ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ሌሎች በንግድ ህጉ የተደነገጉ ተገቢነት ያላቸዉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 32. ሌሎች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎችና የግብይት መድረኮች

1/ ባለስልጣኑ ለሌሎች በአክሲዮን ኩባንያነት ለሚቋቋሙ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያዎች፣ ወይም ለተዛማጅ ገበያዎች ወይም ላልተማከሉ የጠረጴዛ ዙሪያ መገበያያ መድረኮች የስራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚሰጠው የስራ ፈቃድ የአነስተኛ የካፒታል መመዘኛን፣ የተገቢነት እና ብቁነት መስፈርትን፣ የስራ እና ስራ አመራር ሁኔታን፣ የብቃት ማስረጃን፣ እና ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎችን በመመሪያ ይደነግጋል፡፡

## 33. በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያና የግብይት መድረኮች ላይ ስለሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) ገበያው በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አቅርቦት እና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ዋጋን ማመላከት እንዳይችል የሚያደርግ ከፍተኛ የግብይት መስተጓጎል ሲከሰት፤

ለ) ተጨባጭ ወይም ተገማች የሆነ ገበያን የማዛባት ድርጊት ሲኖር፤

ሐ) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ወይም ኢንቬስተሮችን ለመጠበቅ ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ ነው ብሎ ባለስልጣኑ ሲያስብ፤ ወይም

መ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግብይት ሊያስቀም የሚችል እርምጃ መንግስት ሲወስድ፤

በጽሁፍ በሚያስተላልፈው ትዕዛዝ መሠረት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም የተዛማጅ ገበያ በትዕዛዙ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ እንዲዘጋ ለመወሰን ይችላል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም በማናቸውም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መደቦች የሚደረጉ ግብይቶች ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ግብይት የሚደረግባቸው ተዛማጅ ውሎች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ወይም የተጓደለ ካለ እንዲስተካከል ለማድረግ፤ ወይም

ለ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መደቦች ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ግብይት የሚደረግባቸው ተዛማጅ ውሎች እንዲሸጡ ለማድረግ፤

አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

3/ ባለስልጣኑ የገበያውን ፈቃድ ለተወሰነ ጊዜ ወይም አንድ ዓይነት ተግባር እስከሚፈጸም ድረስ ሊያግድዉ ይችላል፡፡ ባለስልጣኑ ይህንን እርምጃ የሚወስደው ገበያው፡-

ሀ) ከተሰጠው የስራ ወሰን/ክልል ወይም ከተፈቀደለት የስራ ዘርፍ ወጭ የሆነ ተግባር ከፈጸመ፤

ለ) ከተሰጠው ፈቃድ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ቅድመ ሁኔታዎች ከጣሰ ወይም ካላከበረ፤

ሐ) የባለስልጣኑን ትዕዛዝ ከጣሰ፤

መ) ባለስልጣኑ የሚጠይቀውን ማንኛውንም መረጃ ካልሰጠ፤

ሠ) ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ከሰጠ፤ ወይም

ረ) የዚህን አዋጅ ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪዎች ድንጋጌ ጥሶ ከተገኘ

ነዉ፡፡:

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚደረግ ገበያውን የማገድ ውሳኔ ከ3 (ሦስት) ወራት በላይ ሊቆይ አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ ካመነ እገዳውን ለተጨማሪ ከሦስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የተወሰነው የሦስት ወር የዕገዳ ጊዜ ሲያበቃ ባለስልጣኑ እንደ አስፈላጊነቱ እገዳውን ሊያነሳ ወይም የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፡፡

6/ ገበያው፤

ሀ) ወደ ሀብት ማጣራት ውስጥ ከገባ ወይም ሂሣቡ ተጣርቶ እንዲዘጋ ትዕዛዝ ከተሰጠ፤

ለ) ለፈቃዱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፤

ሐ) ፈቃዱን ለመመለስ ካመለከተ እና ማመልከቻዉ ተቀባይነት ካገኘ፤

መ) ከዚህ በፊት የፈቃድ እግድ ያስከተለበትን ጥፋት ደግሞ ከሰራ፤ ወይም

ሠ) በሌላ በማናቸውም ምክንያት ፈቃዱን ይዞ ለመቀጠል ብቁ እና ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ

ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

7/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ፈቃዱን ለመሰረዝ ከመወሰኑ በፊት ባለፈቃዱ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን በደብዳቤ እንዲያቀርብ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

8/ ባለፈቃዱ ያቀረበው ተቃውሞ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም ባለፈቃዱ የባለሥልጣኑ ማስታወቂያ ደብዳቤ በደረሰው በ30 (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካላቀረበ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

9/ ባለሥልጣኑ የገበያውን ፈቃድ የሰረዘበትን ውሳኔ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

10/ የፈቃዱ መሰረዝ ውሳኔ በጋዜጣ ከወጣበት ወይም ባለሥልጣኑ ከሚወስነው ሌላ ማናቸውም ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 34. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ስራ አመራር

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ስራ የሚመራው በገበያው ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚመረጥ እና በባለስልጣኑ ይሁንታ በሚሾም የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገዉ ቢኖርም፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሹመት የሚፀድቀዉ የባለስልጣኑን ይሁነታ ካገኘ በኋላ ነዉ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቀርበውለት ባለስልጣኑ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካልገለጸ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ የባለስልጣኑን ይሁንታ እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

4/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በኃላፊነት ዘመኑ ሁሉ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) መልካም ስምን የሚያጎድፍ ወይም እምነት የማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ አለመገኘት፤

ለ) የመጨረሻ የመክሰር ውሳኔ ያልተሰጠበት መሆን፤

ሐ) መልካም ስምና ዝናውን መጠበቅ፤ እና

መ) በፋይናንስ፣ በስራ አመራር፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ልምድ እና ብቃቱን በቀጣይነት ማሻሻል፡፡

5/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ገበያው ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተመስርተው የወጡትን ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲሁም የራሱን የገበያውን ውስጠ-ደንቦች አክብሮ መስራቱን ማረጋገጥ እና፡-

ሀ) የገበያውን አጠቃላይ ስራዎች በበላይነት መቆጣጠር፤ እና

ለ) ተገቢውን የፋይናንስ ስራ አመራር መዋቅር እና ሂደቶች በመፍጠር የገበያውን አመራር በበላይነት መከታተል፤

አለበት፡፡

6/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የዚህ አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ተመስርተው የወጡት ደንቦች እና መመሪያዎች ድንጋጌዎች ጥሰቶች ሲፈጸሙ በጋራ እና በተናጠል ኃላፊነት የመወሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡

7/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በባለስልጣኑ ይሁንታ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾሙ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ዋና ስራ አስፈጻሚዎች ይኖሩታል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት የዋና ስራ አስፈጻሚ ሹመት ቀርቦለት ባለስልጣኑ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካልገለጸ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የዋና ስራ አስፈጻሚ ሹመት የባለስልጣኑን ይሁንታ እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

9/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢን እና የዋና ስራ አስፈጻሚን ስልጣኖች ደርቦ መያዝ የተከለከለ ነው፡፡

## 35. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ዉስጠ-ደንቦች

በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ለገበያው እና በገበያው ለሚካሄድ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አስተዳደር፣ አሠራር፣ አመራር እና ቁጥጥር ተገቢ እና አስፈላጊ የሆኑ ዉስጠ-ደንቦችን እና ሥነ-ሥርዐቶችን ማውጣት ይኖርበታል፡፡

## 36. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ኃላፊነቶች

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ለሚከተሉት ጉዳዮች ኃላፊነት ይኖሩበታል፡-

1/ ፍትሃዊነትን፣ ቅልጥፍናን፣ ግልጽነትን እና የኢንቬስተሮች ጥበቃን እንዲሁም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የቁጥጥር ማዕቀፍ መከበሩን ለማረጋገጥ ገበያውን እና አባላቱን በቅርበት መከታተል፣ ቅኝት ማድረግ እና በበላይነት መከታተል፤

2/ በገበያው ላይ የሚፈጠሩ ያለመግባባቶች የሚፈቱበት ስነ-ስርዓት እና የይግባኝ አሰራር፣ ከገበያው አሰራር ጉድለት ጋር የተያያዙ የቴክኒክ ዘዴዎች እና አሰራሮች፣ የሪኮርድ አያያዝ ዘዴ፣ የህግ ጥሰት ስለመኖሩ ያሉ ጥርጣሬዎች ላይ የሚቀርብ ሪፖርት፣ እንደተፈጻሚነቱ የደንበኞችን ገንዘቦች እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ስለሚጠበቁበት አግባብ እንዲሁም ስለግብይት ውሎች አፈጻጸም እና የክፍያ መረጃ የሚሰጥበት ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፤

3/ የገበያ መድረኩ ያላስፈላጊ የዋጋ መዋዠቅን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው የግብይት መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ማለትም የግብይት ማስቆሚያ፣ የዋጋ መዋዠቅ ማቋረጫ ዘዴዎች፣ እንዲሁም የዕለት ጣሪያ እና ወለል መቆጣጠሪያዎች እና ሌሎች የግብይት መቆጣጠሪያዎች እንዲኖሩት ማድረግ፤

4/ በገበያው ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ላይ ከፍተኛ ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ መልስ ያላገኙ የመሸጥ ወይም የመግዛት ግብዣዎችን ወይም ያልተከፈሉ ዕዳዎች ወይም ያልተጠናቀቁ ግብይቶችን የቅርብ ክትትል የሚደረግበት ዘዴ ማበጀት፤

5/ የግብይት አፈጻጸም ውስጠ-ደንቦችን እና የግብይት ትዕዛዞች የሚተላለፉበትን አሰራር ባለስልጣኑ እና የገበያ ተዋናዮች በግልጽ እንዲያውቁት መደረጉን እና ለሁሉም ተሳታፊዎች ወጥነት ባለው መንገድ ተፈጻሚ መሆኑን ማረጋገጥ፤

6/ ለሁሉም ተሳታፊዎች ከኤሌክትሮኒክ መገበያያ ዘዴው ጋር እንዲተሳሰሩ እና የሚፈጥሩትን ትስስር ሳይቋረጥ እንዲያስቀጥሉ እኩል ዕድል መስጠት፤

7/ በተለይም አባላት ተገቢ የስጋት ደረጃ ገደባቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችላቸውን በራሱ የሚሰራ ቅድመ-ግብይት መቆጣጠሪያን ተግባራዊ ማድረግን ጨምሮ ፍትሃዊና ትክክለኛ ግብይት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት መፍጠር እና ተግባራዊ ማድረግ፤

8/ ለሁሉም የገበያ ተዋናዮች የግብይት ውስጠ-ደንቦችን እና አሰራሮችን እንዲያውቁ እኩል ዕድል መስጠት፤

9/ ለገበያው አባላት አስፈላጊ የቅድመ ግብይት እና የድህረ ግብይት መረጃዎችን በቀጥታ ማስራጨት ወይም ቀጥታ ተደራሽነት እንዲኖረው ማድረግ፤

10/ ከስራው ጠባይ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን የሚረዳ የስራ አመራር እንዲኖር ማድረግ፤

11/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው፣ በአባላቱ፣ በባለ አክሲዮኖቹ ወይም በስራ አመራሩ መካከል የጥቅም ግጭት ሲኖር የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም፤

12/ ባለስልጣኑ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት አገልግሎቶቹን መስጠት እና ሥራውን ማከናወን፤

13/ ስራዎቹን፣ አሰራሮቹን፣ እና የአባላቱን ስነ ምግባር በገበያው ውስጠ-ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ እና አሰራሮች መሠረት መምራት እና ማቀናጀት፤

14/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የተመዘገቡ ኩባንያዎችን እና ሰራተኞቻቸው አሰራሮች እና አተገባበሮች ተገቢ በሆኑ ደንቦች መሠረት መካሄዳቸውን መቆጣጠር፤

15/ በሕግ ካልተጠየቀ ወይም እንዲያሳትም ወይም እንዲያሳውቅ ካልተገደደ በቀር በቁጥጥሩ ስር ያሉትን ማንኛውንም አባላቱን እና ደንበኞችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ሚስጢራዊነት መጠበቅ፤ ለባለስልጣኑ ወይም በባለስልጣኑ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በቀር እነዚህን መረጃዎች አሳልፎ አለመስጠት፤

16/ የቅድመ ግብይት መረጃዎች፣ የድህረ ግብይት መረጃዎች፣ እና ስለተጠናቀቁ ግብይቶች መረጃዎች ለሁሉም የገበያ ተዋናዮች ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ የሚደርስበትን ውስጠ-ደንቦች ከነመመዘኛዎቻቸው ማውጣት።

## 37. ለባለስልጣኑ መረጃ ስለመስጠት፣ ሪፖርት ስለማድረግ፣ እና እገዛ ስለማድረግ

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ከሥራው ወይም ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ጋር በተያያዘ ምላሾች እና መረጃዎች መስጠትን ወይም ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የተጣሉበትን ተግባሮች እና ግዴታዎች በአግባቡ ለመፈጸም የሚጠይቃቸው ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ጨምሮ ባለሥልጣኑ ሥራውን እና ተግባሩን ለማከናወን ምክንያታዊነትን መሠረት አድርጎ ለሚያቀርበው ጥያቄ እገዛ ማድረግ አለበት፡፡

2/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፡-

ሀ) ማንኛውም አባሉ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውን ውስጠ-ደንቦች ወይም የገንዘብ ሀብቶቹን መመሪያዎች የማያከበር ከሆነ፤

ለ) አባሉ ግዴታዎቹን ለመወጣት አቅም እንደሌለው ወይም የአባሉ ተገቢነት ላይ ችግር እንዳለ የሚያመለክት የተዛባ የሂሳብ አያያዝ ወይም ሌላ ትክክለኛ ያለሆነ አሰራር መኖሩን ሲገምት፤ ወይም

ሐ) አባሉ ላይ ወይም ስራ አከናዋኝ ላይ ወይም በስሩ በሚሰሩት ሰዎች ላይ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወሰድ

ጉዳዩን ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ የገበያው የዳይሬክተሮች ቦርድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሐ) መሰረት በማንኛውም አባሉ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወሰድ የተከሰተውን ጥፋት ዝርዝር፣ የሂደቱን ዝርዝር እና የቅጣቱን ዓይነት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ሰነዶች ቅጂዎችም በሙሉ ለባለስልጣኑ መላክ አለባቸው፡፡

## 38. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ዉስጠ-ደንቦችን ስለማሻሻል

1/ ዉስጠ-ደንቦቹን በመሰረዝ፣ በመለወጥ ወይም በመጨመር ለማሻሻል የሚፈልግ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የታሰበውን የማሻሻያ ረቂቅ በቅድሚያ ለባለስልጣኑ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት፡፡

2/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የቀረበለትን የማሻሻያ ሀሳብ በተቀበለ በ28 (ሃያ ስምንት) ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የቀረበውን የዉስጠ-ደንብ ለውጥ ሃሳብ ውድቅ ማድረጉን በጽሁፍ ሊያሳውቅ ይችላል፤ ይህ ከሆነ ለውጡ ቢደረግም የሕግ ውጤት አይኖረውም፡፡

3/ የዉስጠ-ደንብ ማሻሻያ ሃሳብ ከቀረበ በኋላ በ28 (ሃያ ስምንት) ቀናት ውስጥ ከላይ የተመለከተው ዓይነት ማስታወቂያ ካልተሰጠ የቀረበው የዉስጠ-ደንብ ማሻሻያ ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

4/ የባለስልጣኑ ቦርድ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውን ከስራው ጋር በተያያዘ የተወሰኑ ድንጋጌዎችን እንዲያካትት ወይም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ውስጠ-ደንቹን እንዲያሻሽል ለማዘዝ ይችላል፡፡

5/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት የተሰጠውን ትዕዛዝ ሳያከብር ከቀረ ወይም በታዘዘው ጊዜ ውስጥ ካላደረገ፡-

ሀ) ባለስልጣኑ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ወጪ የታዘዘውን የዉስጠ-ደንብ ዝግጅት ወይም የዉስጠ-ደንብ ማሻሻያ በራሱ ሊያደርግ ይችላል፤ እና

ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውም በዚህ መንገድ የተሻሻሉትን ውስጠ-ደንቦች አክብሮ እንዲሰራባቸው ይገደድበታል፡፡

# ክፍል አምስት
# የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ

## 39. የፈቃድ አሰጣጥ

1/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ፈቃዱ በባለስልጣኑ ሳይፀድቅለት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ማቋቋም፣ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማስቀመጥ፣ ክፍያዎችን የማጣራትና የመፈፀም ወይም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸዉን አገልግሎቶችን መስጠት አይችልም፡፡

2/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ፈቃድ የሚሰጠው የዝቅተኛ ካፒታል መስፈርትን፣ የብቃትና ተገቢነት መስፈርትን፣ የስራ እና ስራ አመራር ሁኔታዎችን፣ የብቃት ማረጋገጫን እና ሌሎች ማናቸውንም በባለስልጣኑ መመሪያ የሚወሰኑ መስፈርቶች ለሚያሟላ የአክሲዮን ኩባንያ ብቻ ነው፡፡

3/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ስለሚሰጥ ፈቃድ ዝርዝር ሁኔታዎችን በሚያወጣው ድንብ ይወስናል፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ሌሎች በንግድ ህጉ የተደነገጉ ተገቢነት ያላቸዉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 40. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ግዴታዎች

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ስራን እንዲሰራ በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ቀጥለው የተመለከቱትን ግዴታዎች መፈጸም አለበት፡-

1/ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት የሚያስፈልገውን ፍትሃዊ እና ውጤታማ የርክክብ እና ክፍያ ስርዓት መዘርጋት፤

2/ ከሚያከናውናቸው ተግባራት እና ከአሰራሩ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን በከፍተኛ የሙያ ብቃት መቆጣጠር፤

3/ ከኩባንያው ጥቅም ይልቅ የሕዝብን ጥቅም እና ከኩባንያው ጋር የሚሰሩ አካላትን ጥቅም ማስቀደም፤

4/ ስራውን ባለስልጣኑ ባጸደቃቸው ዉስጠ-ደንቦች መሠረት ማከናወን፤ እና መምራት፤

5/ በባለስልጣኑ ወይም በፍርድ ቤቶች ይፋ እንዲደረግ ከተጠየቀው ውጭ ያሉ በእጁ የሚገኙ መረጃዎችን ሚስጢራዊነት መጠበቅ፤

6/ ባለስልጣኑ ባጸደቀው ወይም ባዘዘው ወይም በወሰነው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው እና ወቅታዊ በሆነ ቴክኖሎጂ እና ራስን በራሱ የሚያሰራ ዘዴን ተጠቅሞ አገልግሎቶችን መስጠት፡፡

## 41. ውስጠ-ደንቦችና ውስጣዊ መመሪያዎች

1/ ባለስልጣኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ርክክብ፣ ክፍያ እና ምዝገባ አሰራርን እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን የሚመለከቱ ውስጠ ደንቦችንና ውስጣዊ መመሪያዎችን እንዲያወጣ ወይም አስቀድሞ ያወጣቸውን ደንቦች ባለስልጣኑ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ እንዲያሻሽል የማዘዝ መብት አለው፡፡

2 የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው የተሰጠውን ትዕዛዝ በታዘዘው ጊዜ ውስጥ ሳያከብር ከቀረ፡-

ሀ) ባለስልጣኑ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው ወጪ የውስጠ-ደንብ ዝግጅት ወይም የዉስጠ-ደንብ ማሻሻያ በራሱ ሊያደርግለት ይችላል፤ እና

ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያውም ባለስልጣኑ ያዘጋጃቸዉን ውስጠ-ደንቦች እና መመሪያዎች አክብሮ እንዲሰራባቸው ይገደድበታል፡፡

3/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ባለስልጣኑ ሳያጸድቅለት እንደ አዲስ ያወጣቸውን፣ ያሻሻላቸውን፣ የሻራቸውን፣ የለወጣቸውን ወይም የጨመራቸውን ውስጠ-ደንቦች በስራ ላይ ሊያውል አይችልም፡፡

4/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አዳዲስ ውስጠ-ደንቦችን የሚያወጣ ከሆነ ስለሚያወጣቸው ደንቦች ወይም ማሻሻያዎች ምክንያት እና ዓላማ እንዲሁም ውስጠ-ደንቦቹ ስለሚያስከትሉት ውጤት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የቀረበለትን አዲስ ዉስጠ-ደንብ ወይም ማሻሻያ ሊያጸድቅ፣ ወይም ላይቀበል ወይም ሊያሻሽል ይችላል፤ ሆኖም ውሳኔውን ከሰጠ በኋላ ቢያንስ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

6/ አንድ ተገበያይ የክፍያ ደንቦች የሚጥስ ከሆነ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው ተገበያዩ ዉስጠ-ደንብ በመጣሱ መቀጫ እንዲከፍል ለማዘዝ ይችላል፡፡

## 42. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ

1/ የሚከተሉት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መመዝገብ አለባቸው፡-

ሀ) ለህዝብ ሽያጭ የሚቀርቡ፤ እና

ለ) በአውጪዎቻቸዉ ፈቃድ ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የማስተላለፍ ዉክልና የተሰጡ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት የሕዝብ ኩባንያዎች እና ሌሎች የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች የሚያወጡትን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዓይነትና የሰነዶቹን ባለቤቶች መረጃ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

## 43. ስለ ጥበቃ እና ሪከርድ አያያዝ

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ በግምጃ ቤቱ ውስጥ ለተቀመጡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ተገቢውን ጥበቃ ማድረግ አለበት፡፡

2/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ግዑዝ-አልባ ተደርገው ከተቀመጡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተያያዘ የሚደረጉ የባለቤትነት ለውጦችን በኮምፕዩተር የተደገፈ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት በመፍጠር በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መመዝገብ እና መያዝ አለበት፡፡

3/ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው የሚይዛቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት መዝገቦች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በሚዘጋጅ ባለቤትነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚመዘገብበት የሂሳብ መዝገብ ስርዓት መተካት አለበት፡፡

4/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰውን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የምስክር ወረቀት የሚተካ እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ለመገበያየት፣ በጠቅላላ ጉባኤ ለመሳተፍ፣ የወለድ እና የትርፍ ክፍያ ለማድረግ፣ ለማስያዝ እና በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡት ደንቦች ወይም መመሪያዎች መሠረት የቅድሚያ እና ሌሎች መብቶችን ለመጠቀም የሚያስችል ሁሉን አቀፍ የምስክር ወረቀት ያዘጋጃል፡፡

5/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ግዑዝ-አልባ የተደረጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ኤሌክተሮኒክ የባለቤትነት ሪከርዶችን ይይዛል፤ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች፣ ባለቤቶች እና ሌሎች ጥቅም አለን የሚሉ አካላት ለሚያቀርቡት ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል፡፡

6/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የተሟላ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ ለማድረግ፣ ዝውውር ለማከናወን፣ እና ተያያዥ መረጃዎችን ለመቀበል እንዲሁም ከተውሶ ስሞች እውነተኛ የሰነድ ባለቤቶችን ስሞች፣ እና የባለቤትነታቸውን መጠን ለመያዝ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምነውን ሁሉ ለማድረግ ይችላል፡፡

## 44. <u>ክፍያ እና ርክክብ</u>

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አባላቱ ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ጋር ተያይዞ ያለባቸውን መብት እና ግዴታ በማጣራት በአባላቱ ስም ግዴታዎችን ይፈጽማል፡፡

2/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ግዴታዎችን የሚፈጽመው ለእያንዳንዱ ርክክብ ክፍያዎችን በመፈጸም ነው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ግብይት በሚፈጸምበት ቀንና ክፍያና ርክክብ በሚደረግበት ቀን መካከል የሚኖረው ጊዜ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው በሚያወጣው ዉስጠ-ደንብ ከተቀመጠው ጊዜ መብለጥ የለበትም፡፡

4/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አባላት መካከል የሚደረግ የርክክብ እና ክፍያ ግዴታዎች አፈጻጸም በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በሚያዝ የሰነዶች ሂሳብ መዝገብ ውስጥ ገቢና ወጪ በማድረግ ይከናወናል፡፡

5/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለቤትነት ከግብይቱ የሚመነጨው የክፍያና ርክክብ ግዴታ ሳይፈጸም ሊተላለፍ አይችልም፡፡

6/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ውስጠ-ደንቦች፡-

ሀ) የርክክብ እና ክፍያ አፈጻጸምን በተመለከተ የሚተገበሩ የአሰራር ደንቦችን እና አካሄዶችን መደንገግ አለባቸው፤ እና

ለ) በራሱ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ላይ እና በኩባንያው ውስጥ በሚሳተፉ አባላት ላይ ሁሉ አስገዳጅ እና ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 45. <u>የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት መተላለፍ የመጨረሻ ስለመሆኑ</u>

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት ዝውውር የመጨረሻ እንዲሆን የሚያስችሉ እና በመዝገብ ከገባ በኋላ እደማይሰረዝ የሚያረጋግጡ ድንጋጌዎች ያሉት የአሰራር ውስጠ ደንቦችን ማውጣት እና ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ውስጠ-ደንቦችን ተከትሎ የተደረገና በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መዝገብ የተመዘገበ የባለቤትነት ዝውውር ሊሰረዝ፣ ሊቀየር፣ ወይም ውድቅ ሊደረግ የማይችል የመጨረሻ ሲሆን በኪሳራ ስነ-ስርዓት፣ ወይም በሌላ ማናቸውም ተመሳሳይ ዓላማ ወይም ውጤት ባለው የሕግም ሆነ ልማድ፣ ወይም የሰነዱን መተላለፍ ለማገድ በሚወጣ ማናቸውም የአስተዳደራዊ መስሪያ ቤት ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊታገድ አይችልም፡፡

3/ ባለስልጣኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት፣ ክፍያ፣ ማጣጣት፣ የኪሳራ ክፍፍል እና አመዳደብ የመጨረሻ ስለሚሆንበት አግባብ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## 46. የካፒታል ገበያ ተሳታፊ መፍረስ ወይም መጠባበቂያ ስምምነት ውስጥ መግባት

ከመክሰር ጋር ወይም ዕዳን ለመክፈል ካለመቻል ጋር በተያያዘ የወጡ ሕጎች ቢኖሩም እንኳን፣ አግባብ ያለው ትእዛዝ ወይም ውሳኔ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈፃሚ ኩባንያ ዘንድ ከመድረሱ በፊት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 መሠረት የመጨረሻ እና የማይሻር የሆነውን የማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ አባል ሂሣብ መጣራት ወይም ወደ መጠባበቂያ ስምምነት መግባት በሂሳብ መዝገብ ወጪና ገቢ መደረግ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ  መተላለፍ የመጨረሻነት ወይም የማይሻር መሆን ላይ ለውጥ አያመጣም።

## 47. ሀብት አጣሪዎች ላይ ተፈጻሚ ስለሚሆኑ ውስጠ-ደንቦችና ስርዓቶች

የኪሳራ ወይም ዕዳን ለመክፈል ካለመቻል ጋር የተያያዙ ሕጎች ቢኖሩም እንኳን፣ የማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ ተሳታፊ የሆነ አካል ቢፈርስ፣ በፍርድ ቤት የመክሰር ውሳኔ ቢሰጥበት ወይም የመጠባበቂያ ስምምነት ውስጥ ቢገባ ከማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ ጋር በተያያዘ የገባበት ግዴታ ወይም ማንኛውም በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጩን የሚያስገድዱ የማጣጣት ውስጠ-ደንቦች እና አፈጻጸማቸው በሀብት አጣሪው ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 48. ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዝውውር እና ክፍያ ግዴታ የሚሰጥ መያዣ

የገበያ አከናዋኝ፣ የገበያ ተዋናይ፣ የክፍያ ተቋም ወይም የማዕከላዊ ተዋዋይ ወገን ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዝውውር ወይም በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ ስራ ጋር በተያያዘ ለተፈጠረ ግዴታ በተሰጠ መያዣ ላይ ያላቸው መብት እና ጥቅም፡-

1/ ክፍያ በማቋረጥ ወይም በኪሳራ ሂደት ወይም ተመሳሳይ ዓላማ ወይም ውጤት ባለው ሕግ ሊደናቀፉ፤ ወይም

2/ በማናቸውም ባለገንዘቦች በማያዣው ላይ ያላቸውን መብት ወይም መፍትሔዎች እዳይሰሩበት በሚያደርግ የእገዳ ድንጋጌ  ወይም ትዕዛዝ ሊገደቡ አይችሉም።

## 49. በመዝገብ የገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መገበያየት የተከለከለ ስለመሆኑ

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ባለስልጣኑ ከፈቀደለት ዓላማ እና አግባብ ውጭ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ መዝገብ የተመዘገቡ ሰነዶችን በራሱ ስም ሊገዛ፣ ባለቤት ሊሆን ወይም ሊገበያይባቸው አይችልም።

## 50. ስለተዋዋይ ወገኖች ስለማሳወቅ

ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ በፍጥነት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡-

1/ በሌላ ወገን ያለ ማንኛውም ግዴታ ፈጻሚ በርክክብና ክፍያ ክንዋኔ ላይ ተፈጻሚ የሆኑ የትኛውንም ውስጠ-ደንቦች አለማክበሩን የደረሰበት እንደሆነ፤

2/ በሌላ ወገን ያለ ግዴታ ፈጻሚ የገንዘብ አቋም እና ግዴታዎቹን የመፈጸም አቅሙ የመዋዠቅ ምልክት እያሳየ መምጣቱ ወይም የማያስተማምን መሆኑ ሲገምት፡፡

## 51. ስራን ስለማስቀጠል እና ከአደጋ ተመልሶ ስለማገገም

1/ በገበያው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል አደጋ፣ ቀውስ ወይም መረበሽ ሲያጋጥም ባለስልጣኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያውን ውስጠ-ደንቦቹን እንዲያሻሽል ወይም እንዲያግድ ለማዘዝ ይችላል፡፡

2/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከባለስልጣኑ የተሰጠውን ትዕዛዝ ካላከበረ ባለስልጣኑ የግብይቶችን ፍትሃዊ አፈጻጸምና የተቀላጠፈ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይቶችን ወይም የተወሰነውን ክፍል ለማስቀጠል አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን እርምጃዎች ሊወሰድ ይችላል፡፡

## 52. በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ፤

ሀ) ከተፈቀደለት የሥራ ክልል ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፤

ለ) ፈቃድ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሁኔታዎችን ጥሶ ከተገኘ ወይም ካላከበረ፤

ሐ) በባለሥልጣኑ የተሰጠውን መመሪያ ካላከበረ፤

መ) በባለሥልጣኑ የተጠየቀውን መረጃ ካልሰጠ፤

ሠ) ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ከሰጠ፤ ወይም

ረ) የዚህን አዋጅ ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪዎች ድንጋጌ ጥሶ ከተገኘ፤

ባለስልጣኑ ፈቃዱን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ባለሥልጣኑ የሚወስነው ሁኔታ እስከሚፈጸም ድረስ ሊያገደው ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረግ እገዳ ከ3 (ሦስት) ወራት መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ ከሦስት ወራት ላልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዳበቃ ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ ባመነው መሠረት እገዳውን ማንሳት ወይም ፈቃዱን መሰረዝ አለበት፡፡

4/ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ፤
 ሀ) ወደ ሀብት ማጣራት ውስጥ ከገባ ወይም ሂሣቡ ተጣርቶ እንዲዘጋ ትዕዛዝ ከተሰጠ፤
 ለ) ለፈቃዱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፤
 ሐ) ፈቃዱን ለመመለስ ካመለከተ እና ማመልከቻዉ ተቀባይነት ካገኘ፤
 መ) ከዚህ በፊት የፈቃድ እግድ ያስከተለበትን ጥፋት ደግሞ ከሰራ፤ ወይም
 ሠ) በሌላ በማናቸውም ምክንያት ፈቃዱን ይዞ ለመቀጠል ብቁ እና ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ

 ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

5/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃዱን ለመሰረዝ ከመወሰኑ በፊት ባለፈቃዱ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን በደብዳቤ እንዲያቀርብ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

6/ ባለፈቃዱ ያቀረበው ተቃውሞ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም የባለሥልጣኑ ማስታወቂያ ደብዳቤ በደረሰው በ30 (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካላቀረበ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

7/ ባለሥልጣኑ የኩባንያውን ፈቃድ የሰረዘበትን ውሳኔ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

8/ የፈቃዱ መሰረዝ ውሳኔ በጋዜጣ ከወጣበት ወይም ባለሥልጣኑ ከሚወስነው ሌላ ማናቸውም ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 53. <u>ቅድሚያ የማግኘት መብት</u>

አንድ ሰው የኪሳራ ውሳኔ ከተሰጠበት፣ ዕዳውን መክፈል ካልቻለ፣ ንብረቱ የሚጣራ ከሆነ ወይም በንብረቱ ላይ ባለአደራ ከተሾመበት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው የርክክብ እና ክፍያ ውስጠ-ደንቦች በሌሎች ስነ-ስርዓቶች ወይም ግዴታዎች ላይ ቅድሚያ ይኖራቸዋል፡፡

## 54. <u>የመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች</u>

1/ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ወይም ሌሎች ተቃራኒ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ብሔራዊ ባንክ የሚከተሉትን ለማድረግ ብቸኛ ስልጣን ይኖረዋል፡-
 ሀ) ለመንግስት ሰነዶች ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤትን የማቋቋም፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ስራውን የማካሄድ፣ የመጠቀም እና የመቆጣጠር፤
 ለ) የመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ አልባ ተደርገው ስለሚቀመጡበት ሁኔታ መመሪያ የማውጣት፤

ሐ) ከማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ፣ ከክፍያ ማጣራትና አፈጻጸም፣ ከርክክብ፣ እና ከመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ጋር የተያያዙ ውስጠ ደንቦችንና ውስጣዊ መመሪያዎችን የማውጣት፤ እና

መ) በራሱ የማዕከላዊው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት የመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የመመዝገብ፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተገለጸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት መተላለፍ የመጨረሻ ስለመሆኑ እና በአንቀጽ 48 መሰረት ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ መተላለፍ እና ክፍያ ዋስትና ስለተሰጡ መያዣዎች የተደነገጉት እንደ አግባብነቱ ለመንግስት ሰነዶችም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 55. <u>ልዩ ስልጣን</u>

በዚህ አዋጅ በተቃራኒ የተደነገጉ ማናቸውም ድንጋጌዎች ቢኖሩም ባለስልጣኑ ከልዩ የውለታ ቃሎች እና ሁኔታዎች ጋር ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ግብይት ለሚደረግባቸው  የግል ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሰነድ ማስቀመጥ እና ክፍያ የማጣራትና የመፈጸም ስራን እንዲሰራ ስልጣን ሊሰጠው ይችላል፡፡

# ክፍል ስድስት
# ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ ስለመስጠት

## 56. <u>ቁጥጥር የሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ተግባራትና አገልግሎቶች</u>

1/ የሚከተሉት የካፒታል ገበያ ተግባራት በዚህ አዋጅ መሰረት ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡-

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መግዛት፣ መሸጥ እና ማሻሻጥ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ምክር፣

ሐ) የውክልና ሽያጭ፣

መ) የገንዘብ (ፈንድ) አስተዳደር፣

ሠ) ከግዥ፣ ከመዋሃድ፣ አንድ ድርጅት የራሱ በሆነ ሌላ ድርጅት ውስጥ ያለውን ድርሻ ከመሸጥ ከመጣመር እንዲሁም ሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛትና መሸጥ የሚጠይቁ የድርጅት ገንዘብ አስተዳደር ተግባራት፣

ረ) ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የመጠበቅ እና የማስተዳደር አገልግሎቶች፣

ሰ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች፣

ሸ) የብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎቶች፤ እና

ቀ) ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር ይደረግባቸዋል ብሎ የሚቆጥራቸው ሌሎች ተግባራት::

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) ሰነደ ሙዓለ ንዋይን በተመለከተ የተሰጠው ምክር በመደበኛ ሥራቸው ሂደት እስካጋጠማቸው ድረስ በሚከተሉት ሰዎች ተፈጻሚ አይሆንም፡-

ሀ) በሚመለከተው የመንግስት አካል በተመዘገበና ዕውቅና በተሰጠው የህግ ባለሙያ፤

ለ) በሚመለከተው የመንግስት አካል በተመዘገበና ዕውቅና በተሰጠው የሒሳብ ባለሙያ ወይም አዲተር፤ እና

ሐ) ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር በተየያያዙ ትንተናዎች ወይም ሪፖርቶች ላይ የሚሰጥ ምክር ታትሞ ለህዝብ የሚቀርብበት እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በተመለከተ የተሰጠው ምክር በመደበኛ የሥራቸው ሂደት ሊያጋጥማቸው የሚችሉ የጋዜጣ፣ የመጽሄት ወይም የሌሎች ወቅታዊ ህትመቶች አታሚዎችና አሳታሚዎች፡፡

3/ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ተግባራት ሊከናወኑ የሚችሉት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ፈቃድ በተሰጣቸው በሚከተሉት ሰዎች ብቻ ነው፡-

ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች፣

ለ) የኢንቨስትመንት አማካሪዎች፣

ሐ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኞች፣

መ) የኢንቨስትመንት ባንክ፣

ሠ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አሻሻጮች፣

ረ) የውክልና አስተዳዳሪዎች/ባላደራዎች፣

ሰ) ገበያ ከፋቾች፣

ሸ) ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች፣

ቀ) የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ተሿሚ እንደራሴ፣ እና

በ) ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ዓላማዎች መሠረት ሊተዳደር የሚገባው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሥራ ነው ብሎ በሚፈርጀው ተግባር የሚሰማራ ወይም የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው፡፡

4/ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ፈቃድ የብቁነትን እና የተገቢነት መሥፈርትን፣ ዝቅተኛውን የካፒታል መጠን፣ የውስጥ አደረጃጀት እና የአደጋ ስጋት አስተዳደር እንዲሁም በባለሥልጣኑ መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች የቁጥጥር እና የበላይ ክትትል መሥፈርቶችን ለሚያሟላ ማንኛውም ሰው ይሰጣል፡፡

5/ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ሥራዎች ለመሠማራት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሕግ ጥስትን ለመከላከል፣ ለመመርመር እና ለማረም የሚያስችል የሕግ ማስከበሪያ ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

6/ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ሥራዎች ለመሠማራት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው አባል የሆነበት ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ለሚያወጣቸው ውስጠ-ደንቦችና ውስጣዊ መመሪያዎች ተገዢ መሆን አለበት፡፡

7/ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ስም ቁጥጥር የሚደረግበትን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሥራ የሚሠራ ሰው ፍቃድ ያለው ተሿሚ እንደራሴ መሆን አለበት፡፡

8/ የተሿሚ እንደራሴነት ፍቃድ ለማውጣት መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ባለስልጣኑ በመመሪያ ያወጣል፡፡

9/ አንድ ሰው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የካፒታል ገበያ ተግባራት ላይ የመሠማራት ፍቃድ ሊሰጠው ይችላል፤ ባለስልጣኑ እንዲህ አይነት ፈቃድ

የሚሰጥባቸውን የውስታ ቃሎችን እና ሁኔታዎችን፣ እንዲሁም የአተገባበር መሥፈርቶችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

10/ ባለስልጣኑ በካፒታል ገበያ ሥራዎች ለመሠማራት ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ዓመታዊ ሪፖርትና ኦዲት የተደረገ የፋይናንስ መግለጫን ጨምሮ ሁሉንም ሥራዎቹን በተመለከተ በየጊዜው ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

11/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (10) ጋር በተያያዘ ባለስልጣኑ የካፒታል ገበያ ስራዎችን ለመስራት ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ሪኮርዶችን በሙሉ ሊገመግም፣ ሊያጣራ፣ የሪኮርዶችን ቅጂ ሊወስድ፣ ወይም ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ቅጂዎችን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 57. ብቁና ተገቢ ሰዎች

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት፣ አንድ ሰው ብቁና ተገቢ መሆኑን ለመመዘን ባለስልጣኑ፡-

ሀ) የገንዘብ አቅምን፣

ለ) ፈቃድ ከሚያመለክትበት ሥራ ጋር ተያያዥ የሆነ በትምህርት ወይም በሌላ መንገድ የተገኘ ሙያዊ ብቃትን ወይም ልምድን፣

ሐ) ሊሰጥ ያሰበውን አገልግሎት በብቃት፣ በታማኝነትና በፍትሐዊነት የመፈጸም ችሎታን፤ እና

መ) የአመልካቹን መልካም ስም፣ ፀባይ፣ በገንዘብ አለመታለል እና ታማኝነትን

ከግንዛቤ ያስገባል፡፡

2/ ለዚህ አዋጅ ዓላማዎች ባለስልጣኑ የብቁነትና የተገቢነትን መመዘኛዎች ሲመረምር በአመልካቹ የቀረበለት ቢሆንም ወይም ባይሆንም በእጁ ያለውን ማናቸውንም መረጃ ከግንዛቤ ሊያስገባ ይችላል፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ዓላማ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) ማመልከቻ ከቀረበበት ሥራ ጋር በተያያዘ በአመልካቹ የተቀጠረ፣ ሊቀጠር የታሰበ ወይም ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው፤

ለ) ሥራውን በሚመለከት እንደ ተወካይ ሆኖ የሚያገለግልን ማንኛውንም ሰው፤

ሐ) አመልካቹ ኩባንያ ከሆነ ማናቸውም ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን፣ የኩባንያው ዳይሬክተር ወይም ሥልጣን ያለውን ሠራተኛ፣ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ ካሉ ኩባንያዎች መካከል የሚመደብ ሌላ ኩባንያ፣ ወይም የኩባንያው ዳይሬክተር ወይም ሥልጣን ያለው ሠራተኛ፤ እና

መ) አመልካቹ የውጭ ሀገር ኢንቨስተር ከሆነ፣ ኢንቨስተሩ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 የተደነገገውን ዝቅተኛ መሥፈርት የሚያሟላ መሆኑን

ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከኩባንያው ጋር በተያያዘ ‹‹ትልቅ ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን›› ማለት በኩባንያው ውስጥ ባሉ አክሲዮኖች ጥቅም ያለው ሆኖ፡-

ሀ) መደበኛ የአክሲዮን ድርሻው ከኩባንያው ካፒታል አምስት በመቶ (5%) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ፤ ወይም በባለስልጣኑ መመሪያ የሚወሰን ሌላ መቶኛ(ፐርሰንት) ያለው፤ ወይም

ለ) ለባለአክሲዮኑ የአምስት ከመቶ (5%) ወይም ባለስልጣኑ የሚወስነውን ሌላ የመቶኛ ባለድርሻ መብት የሚያሰጠው፣ ወይም የነዚህን ያህል ባለድርሻዎችን መብት የመቆጣጠር ስልጣን የሚያሰጠው

ነው፡፡

## 58. የፈቃድ ማመልከቻ

1/ ፈቃድ ለማግኘት ለባስልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በሚዘጋጀው ቅጽ ተሞልቶ፣ ከሚጠየቀው ክፍያ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

2/ ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ከሆነ፣ አስቀድሞ የተሰጠው ፈቃድ ጊዜው ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት፡፡

3/ አመልካቹ ባለስልጣኑ ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ እንዲቀርብ የሚፈልገውን ማናቸውንም ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

## 59. የፈቃድ ወይም የፈቃድ እደሳት ጥያቄን ስለመከልከል

1/ ቁጥጥር የሚደረግበት የካፒታል ገበያ ተግባርን ለማከናወን የፈቃድ ወይም ፈቃድ የማደስ ጥያቄ የሚያቀርብ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ፈፅሞ ከተገኘ ባለስልጣኑ ፈቃዱን ወይም የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄዉን ሊከለክል ይችላል፡-

ሀ) አሳሳች መረጃ ለባለስልጣኑ ካቀረበ፤

ለ) ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት ለባለሥልጣኑ ሊቀርብ የሚገባ ወሳኝ የሆነን ጉዳይ ወይም መረጃ ሳይገልጽ ከቀረ፤

ሐ) የብቁነትና የተገቢነት መመዘኛን፣ አነስተኛውን የካፒታል መጠን፣ የውስጥ አደረጃጀትና የስጋት አመራርን እና በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ፈቃድ ለማግኘት የሚጠየቁ የቁጥጥር መስፈርቶችን ካላሟላ፤

መ) ከፈቃድ ጋር የተያያዘን ሥራ ለማከናወን የአዕምሮ ወይም የአካል ብቃት የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ፤ ወይም

ሠ) የዚህን አዋጅ ወይም አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌን ጥሶ መገኘቱ ከተረጋገጠ፡፡

2/ ባለስልጣኑ ለአመልካቹ ወይም ለባለፈቃዱ የመሰማት ዕድል ሳይሰጥ ፈቃድ ሊከለክል ወይም አላድስም ሊል አይችልም፡፡

## 60. ፈቃድን ስለማገድ

1/ ቁጥጥር የሚደረግበት የካፒታል ገበያ ተግባርን ለማከናወን ፈቃድ ያለዉ ማነኛዉም ሰዉ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ ወይ በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የተመለከቱትን የባለፈቃድ ግዴታዎችን ካልተወጣ፤
ለ) በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ካልሰጠ፤
ሐ) ፈቃዱ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሁኔታዎችን ወይም ገደቦችን ወይም የዚህን አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌን ተላልፎ ወይም ጥሶ ከተገኘ፤
መ) ፈቃድ ከተሰጠው ወይም ፈቃዱ ከታደሰለት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 12 (አሥራ ሁለት) ወራት ውስጥ ፈቃድ ያገኘበትን ሥራ ካላከናወነ፤ ወይም
ሠ) በሥራ የሚገናኛቸውን ወይም የበታች ሠራተኛውን የዚህን አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎችን በሚጥስ መንገድ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ ካልቻለ

ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንጽ (1) ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ የእገዳውን ምክንያት እና ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ለእገዳው ምክንያት የሆነውን ጉድለቶች ለማስተካከል መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ለባለፈቃዱ በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

3/ ባላስልጣኑ ለአመልካቹ ወይም ለባለፈቃዱ የመሰማት እና ፈቃዱ መታገድ እንደሌለበት ምክንያቱን በጽሑፍ እንዲገልጽ ዕድል ሳይሰጠው ፈቃዱን ሊያግድ አይችልም፡፡

4/ ፈቃዱ በባለሥልጣኑ የታገደበት ማንኛውም ሰው የፈቃዱ እገዳው ከፀናበት ቀን ጀምሮ ቁጥጥር በሚደረግበት በማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ አይችልም፡፡

## 61. <u>ፈቃድን ስለመሰረዝ</u>

1/ ባለሥልጣኑ በዚህ ክፍል የተመለከተውን ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች መሰረዝ ይችላል፦
ሀ) ፈቃዱ ሐሰተኛ ወይም የተሳሳተ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
ለ) ባለፈቃዱ በራሱ ምርጫ ቁጥጥር የሚደረግበትን ሥራ ማከናወን ካቆመ፤
ሐ) ባለፈቃዱ ለፈቃዱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፤
መ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ላልተፈቀደ ተግባር ወይም ዓላማ ከተጠቀመበት፤
ሠ) ባለፈቃዱ ከዚህ በፊት የፈቃድ እግድ ያስከተለበትን ጥፋት ደግሞ ከሰራ፤ ወይም
ረ) ባለፈቃዱ ኪሣራ ከታወጀበት ወይም ክፍያ መክፈል ካቆመ፡፡

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃዱን ለመሰረዝ ከመወሰኑ በፊት ባለፈቃዱ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን በደብዳቤ እንዲያቀርብ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3/ ባለፈቃዱ ያቀረበው ተቃውሞ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም የባለሥልጣኑ ማስታወቂያ ደብዳቤ በደረሰው በ30 (ሰላሣ) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ካላቀረበ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

4/ ባለሥልጣኑ የኩባንያውን ፈቃድ የሰረዘበትን ውሳኔ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

5/ የፈቃዱ መሰረዝ ውሳኔው በጋዜጣ ከወጣበት ወይም ባለሥልጣኑ ከሚወስነው ሌላ ማናቸውም ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

6/ ፈቃዱ ከተሰረዘ ወይም ባለፈቃዱ ግዴታውን መወጣት ካልቻለ፣ ባለሥልጣኑ በባለፈቃዱ ወይም በባለፈቃዱ ስም በሦስተኛ ሰው የተያዘን ሀብት በሌላ ሰው ይዞታ ሥር እንዲሆን ወይም ቁጥጥር እንዲደረግበት ባለፈቃዱን፤
   ሀ) የደንበኛውን የባንክ ሂሣቦች ወደ ሌላ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አገልግሎት አቅራቢ እንዲያዛውር፤ እና/ወይም
   ለ) ተቆጣጣሪ፣ ንብረት ጠባቂና አጣሪ ወይም ሌላ አስተዳዳሪ እንዲሾም፤
   ሊያደርገዉ ይችላል፡፡

## 62. <u>የራሱን በራስ ተቆጣጣሪ ድርጅት አባል ስለመሆን</u>

በዚህ ክፍል ለአመልካቾች የተሰጡት መብቶች ቢኖሩም፣ ባለስልጣኑ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፍቃድ ለማውጣት ወይም ለማሳደስ የራሱን በራስ ተቆጣጣሪ ድርጅት አባል እንዲሆኑ የሚያስገድድ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 63. <u>የሒሳብ መዝገብ ቅኝት እና የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት</u>

1/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚመለከተው የመንግስት አካል በሚጠይቀው የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መሠረት የሒሳብ መዝገብ ስርዓት መዘርጋት እና ከእርሱ ጋር የተያያዙ ግብይቶችን ወይም የባለቤትነት ዝውውሮችን በትክክልና በዝርዝር በሂሳብ መደቦች መመዝገብና መያዝ አለበት፡፡

2/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው መዝገቦቹን፣ ሰነዶቹን እና የሒሳብ መግለጫዎችን ከተዘጋጁበት ቀን ጀምሮ ለ10 (አስር ዓመት) ወይም ከደንበኛው ጋር ሙግት ውስጥ የገባበት ጉዳይ ካለ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የበለጠውን ያህል ጊዜ ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡ በዚህ ወቅትም ለምርመራ ከተፈለጉ መቅረብ አለባቸው፡፡

3/ የተጠቀሱት ሰነዶች በባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ ስራውን እንዲያከናውን በሚመድበው ማናቸውም ሰው በማናቸውም ጊዜ ፍተሻ ወይም ምርመራ ይካሄድባቸዋል፡፡

4/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የደንበኞቹን ማንነት መዝግቦ የመያዝ፣ እንዲሁም ገንዘብና ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር በተያያዘ ከድለላ እና ከባንክ ሒሳቦች የገቡበትንና የወጡበትን ክትትል ለማድረግ በሚያስችል መልኩ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

5/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሂሳብ መዝገብ ቅኝትን በተመለከተ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና ለሚከተሉት ተገዢ መሆን አለበት፡-

ሀ) በበላይነት ለመከታተል ለስጋት አስተዳዳር እንዲሁም የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችሉ የዉስጥ መመሪያዎችንና አሠራሮችን ማዘጋጀት፤

ለ) ሥራዎችን ከሚመለከተው ክፍል በተገኘ አጠቃላይ ወይም ልዩ ፈቃድ መሠረት መፈጸም፤

ሐ) ከሚመለከተው ክፍል በተገኘ አጠቃላይ ወይም ልዩ ፈቃድ መሠረት ሀብት የማስወገድ ሂደት ነጻነትን ማረጋገጥ፤

መ) የተመዘገቡ ሀብቶችን፣ በአስፈላጊው ጊዜ በማስተያየት የጎላ ልዩነት ከታየ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፤ እና

ሠ) የሚመለከተው የመንግስት አካል ባስቀመጠው አሠራር መሠረት የፋይናንስ መግለጫ ማዘጋጀት በሚያስችል መልኩ ግብይቶችን/ሂሳቦችን መመዝገብ፡፡

## 64. የዉጭ ኦዲተሮች ስያሜ

1/ እያንዳንዱ ፈቃድ ያለው ሰው በባለስልጣኑ የፀደቀ የዉጭ ኦዲተር መሰየም አለበት፡፡

2/ አንድ ሰው ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የውጭ ኦዲተር ሆኖ መሰየም የማይችልባቸው ሁኔታዎች፡-

ሀ) ለባለ ፈቃዱ ሰው የአክሲዮን ባለድርሻ፣ ዳይሬክተር ወይም ሰራተኛ ከሆነ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ(ሀ) ከተዘረዘሩት በአንዱ ምድብ ላለ ሰው የትዳር ጓደኛ ከሆነ ወይም በጋብቻም ሆነ በስጋ አንደኛ ደረጃ ዝምድና ካለው፤ ወይም

ሐ) የኦዲተሮቹ ድርጅት ባለድርሻ ወይም የኦዲት ቡድን አባል በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ሥር ከተጠቀሱት በአንዱ የሚወድቅ የሆነ እንደሆነ፡፡

3/ ባለስልጣኑ ፈቃድ ለተሰጣቸው ግለሰቦች የውጭ ኦዲተር ሆነው ሊሰየሙ የሚችሉ ባለሙያዎች ሊኖራቸው ስለሚገባ ዝቅተኛ ሙያዊ ዕውቀትና ልምድ በየጊዜው መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

# ክፍል ሰባት
# የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት

## 65. የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ስለማቋቋም

በባለስልጣኑ ውሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በይግባኝ መርምሮ የሚወስን የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት (ከዚህ በኃላ ‹‹አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት›› እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

## 66. የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ስልጣን

አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በባለስልጣኑ ወይም የባለስልጣኑን ተግባርና ስልጣን በሚያስፈጽም ሰው በተላለፈ ውሳኔ ላይ የቀረበን ይግባኝ የመስማትና የመወሰን ስልጣን አለው።

## 67. የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ አባላት ሹመት

1/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አምስት አባላትን ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ይሾማሉ።

2/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ አባላት ከሚከተሉት የተውጣጡ ይሆናሉ፡-

- ሀ) የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ማገለገል የሚያስችል ብቃት ያላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፤ እና
- ለ) የህግ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣ የንግድ ሥራ ወይም የፋይናንስ ወይም የሒሳብ አያያዝ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ሌሎች ሦስት አባላት።

3/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ አባል፡-

- ሀ) የሙሉ ጊዜ ወይም የትርፍ ጊዜ አባል ተደርጎ ሊሾም ይችላል፤
- ለ) የሹመቱ የመጀመሪያ የሥራ ዘመን 5 (አምስት) ዓመት ሆኖ፣ ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን በድጋሚ ሊሾም ይችላል፤ እና
- ሐ) በስራው በሚቆይበት ጊዜ ክፍያውና የሙያ አበሉ፣ መንግስት በሚወስነው መሰረት ይሆናል።

## 68. ለአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ አባልነት ብቁ አለመሆን

አንድ ሰው፡-

1/ መክሰሩ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠበት፤

2/ የባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ ፈቃድ ለሰጠው ሰው ሰራተኛ ከሆነ፤ ወይም

3/ በማንኛውም ህግ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ከ6 (ስድስት) ወር የበለጠ እስራት ከተፈርደበት

የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ አባል መሆን አይችልም።

## 69. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ አስተዳደር

1/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ የፍርድ ቤቱን አስተዳደራዊ ጉዳዮች ይመራል።

2/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር እና በሰብሳቢው የሚወሰን ሌሎች መሰል ሠራተኞች ይኖሩታል።

## 70. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ በጀት እና የሂሳብ መዝገብ

1/ የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

2/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የተሟላና ትክክለኛ የሒሳብ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

3/ የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የሒሳብ መዝገቦችና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደረል ዋና ኦዲተር ወይም በፌደራል ዋና ኦዲተር በሚመደብ ኦዲተር ይመረመራል፡፡

## 71. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ዓመታዊ ሪፖርት

1/ የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤት ሰብሳቢው በየበጀት ዓመቱ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱን ጉዳዮች የሚመለከት ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለየበጀት ዓመቱ የሚዘጋጀው ሪፖርት የበጀት ዓመቱ ባለቀ በ3 (ሦስት) ወር ጊዜ ውስጥ ለጠቅላይ ሚንስትሩ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 72. ይግባኝ ስለመጠየቅ

1/ ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ ውሳኔ ላይ ለአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ መጠየቅ ከፈለገ፣ ውሳኔው ከተገለጸለት በኋላ ባሉ በ28 (ሃያ ስምንት) ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማሳወቂያ ለሬጅስትራር ፋይል በማድረግ እና የተወሰነውን ክፍያ በመፈጸም ማመልከት ይችላል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ ይግባኝ በወቅቱ ያልተጠየቀበት አሳማኝ ምክንያት ካለና ከዚያም በኋላ ያለምንም መዘግየት ይግባኙ እንደተጠየቀ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ካመነ የተጠቀሰው ጊዜ ካለፈም በኋላ ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡፡

3/ የይግባኝ ማሳወቂያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በሚጠይቀው አቀራረብ መሠረት ለይግባኝ ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች ለይቶ የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

4/ ባለስልጣኑ የይግባኝ ማስታወቂያው በደረሰው በ7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ ይግባኝ ከተጠየቀበት ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሰነዶችን ቅጂ ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ መላክ አለበት፡፡

## 73. የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ አሠራር

1/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሰብሳቢው ከአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ችሎቶች የአንዱ አባል ሆኖ ያገለግላል፡፡

2/ በይግባኝ የተነሱትን ጭብጦች ከግምት ውስጥ በማስገባት የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ተገቢ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱን አባል ወይም አባላት ይግባኙን እንዲሰሙ ይመድባል፡፡

3/ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን፣ ብይኑን፣ ትእዛዙን እና የችሎት አካሄዱን ለማስፈጸም በፍትሐ ብሔር ስነ-ስርዓት ህግ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ስልጣን ይኖረዋል፡፡

## 74. <u>የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ</u>

1/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ይግባኝ በመስማት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ በተጠየቀ በ60 (ስልሳ) ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3/ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት እና ለፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለተከራካሪ ወገኖች የጽሑፍ ማሳወቂያ በመስጠት የይግባኝ መወሰኛ ጊዜውን ከ30 (ስላሳ) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

4/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተመለከቱትን አለማክበሩ በፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ተቀባይነት ሊያሳጣው አይችልም፡፡

5/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ይግባኝ ከተመለከተ በኋላ፡-
- ሀ) የመጀመሪያውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ እንዳለ ሊያፀናው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው፤
- ለ) ትክክለኛ ነው ብሎ በወሰነው አቅጣጫ ጉዳዩን እንደገና እንዲያየው ወደ ባለስልጣኑ ሊመልሰው፤ ወይም
- ሐ) ትክክለኛ ነው ብሎ የሚያምነውን ማናቸውም አይነት ሌላ ትእዛዝ ሊስጥ

ይችላል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 5 (ሀ) መሰረት አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ከሻረ፣ ትእዛዙን ወይም ውሳኔዉን ራሱ ትክክለኛ ነው ብሎ ባመነበት ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ሊተካዉ ይችላል፡፡

7/ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ የይግባኙን ውሳኔ ቅጂ፣ ውሳኔውን በሰጠ በ7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ ለባለጉዳዮቹ እንዲደርሳቸው ማድረግ አለበት፡፡

8/ የአስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ለውሳኔ ያበቁትን ምክንያቶች እንዲሁም ጥያቄ ባስነሱ ጭብጦች ላይ የተደረሰበትን ግኝት፣ የማስረጃውን ዋቢ ወይም ሌሎች ለግኝቱ መሠረት የሆኑ ፍሬነገሮችን ማካተት አለበት፡፡

9/ በይግባኙ ላይ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ወይም አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤቱ በውሳኔ ማሳወቂያው ላይ ከሚገልጸው ሌላ ማናቸውም ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 75. ወደ ፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ስለመጠየቅ

በአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ አካል ውሳኔውን ባወቀ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በህግ ጉዳይ ላይ ብቻ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

# ክፍል ስምንት
# ለህዝብ ሽያጭ ማቅረብና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት

## 76. የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ

1/ ለህዝብ የሚሸጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለሽያጭ ወይም ለገበያ ከመቅረቡ በፊት በባለስልጣኑ መመዝገብ አለበት፡፡

2/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪ ወይም ተወካዩ ለዚሁ ተብሎ በባለስልጣኑ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በመፈረም የተወሰነውን ክፍያ በመክፈል የምዝገባ መግለጫውን ለባለስልጣኑ ማስገባት አለበት፡፡

3/ ባለስልጣኑ መግለጫን ለማስመዝገብ የሚጠየቀውን መረጃ በመመሪያ ይወስናል፡፡

4/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አይነቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡-

ሀ) በኢትዮጵያ መንግስት ለሽያጭ በቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤
ለ) በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤
ሐ) በኪሳራ ወይም ክፍያ መፈፀም ባለመቻል በሚሸጡ የሃብት አሰተዳዳሪ ኩባንያዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤
መ) በግል ለሽያጭ በሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፤ እና
ሠ) ባለስልጣኑ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ከምዝገባ ነጻ በተደረጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፡፡

5/ በግል ለሽያጭ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለህዝብ ለሽያጭ አይቀርቡም፡፡

6/ ባለስልጣኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በግል ለሽያጭ የሚቀርቡበትን መሥፈርቶች በመመሪያ ይወስናል፡፡

7/ ባለስልጣኑ የታዳጊ ድርጅቶችን የምዝገባ መግለጫ መሥፈርቶችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

8/ ባለስልጣኑ ባልተማከለ ጠረጴዛ ዙሪያ የሚደረጉ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽያጭ ለማካሄድ የሚጠየቁ የምዝገባ መግለጫ መሥፈርቶችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 77. በኩባንያዎች ለሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መግለጫ

1/ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪ ማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለህዝብ ለሽያጭ ለማቅረብ ሰነዱን ከማውጣቱ ወይም ከማስተዋወቁ በፊት የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን በባለልጣኑ ማስፀደቅ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው መግለጫ ትክክለኛ፣ የሚገባውን ያህል ግልጽ፣ የተሟላ፣ ምክንያታዊ በሆነ ደረጃ የሚፈለገውን ለይቶ የሚያቀርብ እና ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ባለስልጣኑ ለህዝብ የሚቀርቡ የሽያጭ ማስታወቂያዎችን ጨምሮ፣ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ የተለዩ መሥፈርቶችን በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

4/ ባለስልጣኑ አንድን የደንበኛ መሳቢያ መግለጫ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊከለክል ይችላል፡-

ሀ) መግለጫው የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች፣ ይህን አዋጅ ወይም ሌሎች በባለስልጣኑ መመሪያዎች እንዲሟሉ የሚጠየቁ መስፈርቶችን ያልተከተለ ከሆነ፤ ወይም

ለ) መግለጫው በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገዥው ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችል የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ ሃሳብ ካለበት፡፡

5/ መግለጫ አውጭው መግለጫውን በባለስልጣኑ መመሪያ በተካተቱት ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት፣ ያለ ክፍያ ለህዝብ ማቅረብ አለበት፡፡

## 78. በቀጣይነት መረጃን ይፋ የማድረግ ግዴታዎች

1/ ለህዝብ የሚቀርቡ ወይም በህዝብ የተያዙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሽያጭ የሚያቀርብ አዉጪ ከራሱ እና፣ ካለ፣ ከተቀጥላ ድርጅቱ ጋር በተያያዘ፡-

ሀ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢውንና የተቀጥላ ድርጅቱን የፋይናንስ አቋም ለመገምገም አስፈላጊ የሆነ፤ እንዲሁም

ለ) በሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የሚገበያይ የሐሰት ገበያ እዳይቋቋም የሚያደርግ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የገበያ ዋጋ ላይ በወሳኝነት ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል፤

መረጃ ለባለሥልጣኑ፣ ለአባላቱ እና የእርሱን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለያዙ በተቻለ መጠን በፍጥነት ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ ማናቸውም ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢዎች በባለስልጣኑ መመሪያዎች፣ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ባወጣቸውና ባለስልጣኑ ባጸደቃቸው ዉስጠ-ደንቦች መሠረት የተመረመረ የሂሳብ መግለጫቸውን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

3/ ባለስልጣኑ የተመዘገቡ ኩባንያዎች በውስጣቸው የሚከሰቱ ማናቸውንም አይነት ጉልህ ለውጦችን በፍጥነት በይፋ እንዲያሳውቁ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4/ ማነኛዉም ሰዉ ይፋ የተደረጉ ወይም የተገለፁ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተቀመጡ ወቅታዊ ህትመቶችን፣ ሪፖርቶችን፣ መረጃዎችን እና የመግለጫዎችን ቅጂዎች ባለሰልጣኑ የሚወስነውን ክፍያ እየከፈለ ማየት ወይም ቅጅ መውሰድ ይችላል፡፡

5/ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አንድ ጊዜ ከወጡ በኂላ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ዋጋ ሊለውጡ የሚችሉ ማናቸውንም መረጃዎች መኖራቸው በአቅራቢው ድርጅት ዳይሬክተር እንደታወቀ፣ አውጪው ወዲያውኑ ለህዝብ በሚሰራጭ ጋዜጣ በሚወጣ ማስታወቂያ እና ለባለስልጣኑ እና ለተመዘገቡባቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ሪፖርት በማድረግ ህዝቡ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አነቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም፣ ባለስልጣኑ ወሳኝነት ያላቸውን መረጃዎች ይፋ ስለማድረግ ተጨማሪ ግዴታዎችን በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 79. <u>በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አሻሻጥ</u>

1/ በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሽያጭ የሚቀርቡት በባለ ልዩ ተልእኮ ተቋም የሚወጡ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

2/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) ወደ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ከሚቀየሩና በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር የተያያዙ በገበያው የሚወጡ ሰነዶችና ተግባራትን፤ እና

ለ) በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢዎችን በሚመለከት፣ ለእያንዳንዱ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምድብ፣ ሰነዱ የተደገፈውን ሀብት የሚመለከት መረጃን በተመለከተ ስለሚወጡት ውስጠ-ደንቦችና ውስጣዊ መመሪያዎች መመሪያ ማውጣት አለበት፡፡

3/ ባለስልጣኑ ሰነዱ የወጣበትንና ለሽያጩ የቀረበበትን ምድብ እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን የደገፈውን ሀብት አይነት ወይም ባለስልጣኑ ተገቢ ናቸው ብሎ የሚላቸውን ሌሎችን ጉዳዮች ከግንዛቤ በማስገባት፣ የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን ወይም የኩባንያውን አላማዎች፣ ስጋት እና የሙዓለ ንዋዮች የውለታ ቃሎች የመሳሰሉት የሚገለፁበትን ሰነድ ይዘት በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

4/ ማናቸውም ሰው በዚህ ክፍል ወይም በባለስልጣኑ ካልፀደቀ በስተቀር በሃብት የተደገፈ ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ወይም ለተወሰኑ ኢንቨስተሮች ለገበያ ሊያቀርብ ወይም እንዲፈርሙ ወይም እንዲገዙ ሊጋብዝ አይችልም፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## ጥቅምን ይፋ ስለማድረግ

### 80. ትርጓሜ

ለዚህ ክፍል ዓላማ ‹‹ጥቅም ያለው ሰው›› ማለት ማንኛውም በግብይት የተመዘገበን ኩባንያን ካፒታል አምስት (5) በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን በቀጥታ፣ በተዘዋዋሪ ወይም ከሌሎች ጋር በመጣመር ድርሻ ያለው ሰው ነው፡፡

### 81. የቀረበ መረጃ

1/ ጥቅም ያለው ሰው ድርሻ ከገዛበት ቀን ጀምሮ በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ የተረጋገጠና የተፈረመ መግለጫ ለባለስልጣኑ፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ግብይት ለሚፈፀምበት ገበያ እና ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ አቅራቢ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰዉን መግለጫ ይዘት ባለስልጣኑ በመመሪያ ይወስናል፡፡

3/ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተመዘገበ ማንኛውም አክሲዮን ኩባንያ፣ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች ስምና በአክሲዮን ድርሻቸው ላይ የሚደረገውን ማናቸውንም ለውጥ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገዉን መረጃ ይፋ የሚደረግበትን አሠራርና ጊዜ በተመለከተ ባለስልጣኑ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

5/ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የተመዘገበበት ገበያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) ይፋ የተደረጉ ጥቅሞችን በተመለከተ የደረሰውን መረጃ መረጃው እንደደረሰው ወዲያውኑ በባለስልጣኑ መመሪያ በተደነገገዉ መሠረት ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

6/ መረጃውን ይፋ የማድረግ ግዴታ የተጣለበት ሰው፣ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ጥቅሞችን ባለማሳወቁ ምክንያት በባለስልጣኑ፣ በገበያው ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርሰው ማናቸውም ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 82. ለውጦችን ስለማሳወቅ

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 81 ይፋ ስለማድረግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጥቅም ያለው ሰውና በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተመዘገበ አክሲዮን ኩባንያ ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው ካፒታል 0.5 በመቶ የሚበልጡ በጥቅም ላይ የተደረጉ ማናቸውንም ለውጦች፣ ለውጡ በተደረገ በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ለተመዘገበበት ገበያ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሪፖርት የማድረጉ ግዴታ፣ የጥቅም ለውጡ እየቀነሰ ሄዶ ጥቅሙ ከካፒታሉ ከ5 በመቶ በታች እስከሚሆን ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡

## 83. ይፋ የማድረጊያ መዝገብ

1/ ማንኛውም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የተመዘገበ አክሲዮን ኩባንያ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተሮችን እና ሥራ አስኪያጆችን የሚመለከት መረጃ ለጠቅላላ ጉባኤው በቀረበው ሪፖርት ውስጥ በተካተተበት አኳኋን ክፍያን፣ ደመወዝን፣ ማትጊያን እና ሌሎችን ጥቅማ ጥቅሞችን ጨምሮ በባለስልጣኑ በሚወሰነው መሠረት መግለጫዎችንና መረጃዎችን ይፋ የሚያደርግበት ልዩ መዝገብ ሊኖረው ይገባል፡፡

2/ ማንኛውም ባለድርሻ አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰዉን መዝገብ በመደበኛ የሥራ ሠዓት የማየት መብት አለው፡፡

# ክፍል አስር
# ለቁጥጥር የሚያበቃ የአክስዮን ግኘ እና ስለ አነስተኛ ባለድርሻዎች መብት ጥበቃ

## 84. ትርጓሜ

ለዚህ ክፍል አላማ ‹‹**ለቁጥጥር የሚያበቃ የግዢ ጥያቄ**›› ማለት አንድን የተመዘገበ ኩባንያ የዳይሬክተሮች ቦርድ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለመቆጣጠር የሚያስችል የግዥ ጥያቄ ማቅረብ፣ ለመግዛት ግፊት ማድረግ ወይም ከመቶኛ አብዛኛውን ባለቤት ለመሆን ጥያቄ ማቅረብ ነው፡፡

## 85. የግዢ ጥያቄ

1/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው፣ በባለስልጣኑ በወጣው መመሪያ ወይም በሌላ ህግ መሠረት ካለሆነ በስተቀር የማናቸውንም ኩባንያ አክሲዮን ለቁጥጥር በሚያበቃ መልኩ መግዛትን በተመለከተ የመግዛት ጥያቄ ማቅረብም ሆነ ክትትል ማድረግ አይችልም፡፡

2/ ለቁጥጥር የሚያበቃ የአክሲዎን ግዥ የሚፈልግ ሰው፣ የግዢ ጥያቄ ማቅረቢያ ሰነዶችን ቅጂ ከሌሎች አግባብነት ካላቸው መረጃዎች ጋር ለባለስልጣኑ፣ ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው እና ለቁጥጥር የሚያበቃ ግዥ ለተጠየቀበት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው ማቅረብ አለበት፡፡

3/ ለቁጥጥር የሚያበቃ የአክሲዎን ግዥ የሚያደርግ ሰው ከባለስልጣኑ ይሁንታ ከማግኘቱ በፊት በግዢው ሂደት ወደ ቀጣዩ ደረጃ መሸጋገር የለበትም፡፡

4/ ባለስልጣኑም ማመልከቻውን እና የግዢ ሰነዶችን በማረጋገጥ ቢዘገይ በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ ዉሳኔ መስጠት አለበት፡፡

5/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) የግዥ ጥያቄው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችንና ተያያዥ የሆኑ ባለስልጣኑ ያወጣቸውን መመሪያዎች የሚጥስ ሆኖ ከተገኘ፤

ለ) ከግዥ ጥያቄው ጋር የማመልከቻ ክፍያዎች ተያይዘው ካልቀረቡ፤

ሐ) የግዥ ጥያቄ አቅራቢው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ባለስልጣኑ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት የሚያስፈልጉ ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ ካልቻለ፤ ወይም

መ) የግዥ ጥያቄው የአክሲዮን ኩባንያው ባለ አክሲዮኖች ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ትክክል ያልሆነ ወይም ያልተሟላ ነገር ከተገኘበት

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ለቀረበለት ማመልከቻ ይሁንታ ሊከለክል ይችላል፡፡

6/ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከአንድ የተመዘገበ ኩባንያ ግብይት እንዲደረግባቸው ከገቡ አክሲዮኖች ከሚያስፈልገው አብላጫ የመቶኛ ድርሻ በላይ የገዛ ሰው ከገዛበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በገበያው ግብይት የሚደረግባቸውን ቀሪ አክሲዮኖች ለመግዛት የግዢ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

7/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 6 ድንጋጌ የሚውል የመቶኛ አብላጫ ድርሻ መጠንን ባለስልጣኑ በመመሪያ ይወስናል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ጎጂ ተጽዕኖ የደረሰበት ማንኛውም ባለአክሲዮን የተመዘገበው ኩባንያ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች አነስተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸውን ባለአክሲዮኖች ጥቅም የሚጎዳ የሆነ እንደሆነ በንግድ ህጉ በተቀመጡ ተገቢነት ባላቸዉ ድንጋጌዎች መሠረት ውሳኔውን መቃወም ይችላል፡፡

9/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6)፣(7) እና (8) በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡-

ሀ) ለህዝብ ጥቅም እና ለተቀሩት ባለአክሲዮኖች ሲባል በሚደረጉ ግዢዎች፤

ለ) ኩባንያው ካፒታሉን በሚያሳድግበት ጊዜ በሚገኝ ተጨማሪ የአክሲዮን ድልድል የተወሰኑ ባለአክሲዮኖች ከመግዛት በመቆጠባቸው ምክንያት መቶኛ ገደብ ሲታለፍ፤

ሐ) ዕዳ (ብድር) እንደገና በመዋቀሩ ወደ አክሲዮን በመቀየሩ ምክንያት የተጠቀሰው የመቶኛ ገደብ ሲታለፍ፤

መ) በውርስ፣ በኑዛዜ ወይም በፍርድ ውሳኔ የተጠቀሰው መቶኛ ሲወሰድ፤ የተጣለው የመቶኛ ገደብ ሲታለፍ፤ እና

ሠ) ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ውስጠ-ደንቦች እና በተካተቱ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች፡፡

10/ ማናቸውም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9(ሀ) መሰረት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የተፈጻሚነት ወሰንን የሚገድብ ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ ምክንያቱ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

11/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 9(መ) አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ግለሰቡ ጭማሪ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ከ2 (ሁለት) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የድርሻውን ሁኔታ ማስተካከል አለበት፡፡

12/ ለቁጥጥር በሚያበቃ መልኩ ግዢ የሚፈጸምባቸው ወይም እንዳለ ተጠቃለው የሚወሰዱበት አክሲዮኖቹን ለሽያጭ ያቀረበ አክሲዮን አውጪ አስተያየቱን እና ለባለአክሲዮኖች የውሳኔ ሃሣቦችን ያካተተ ምላሽ የሽያጭ ማቅረቢያው ማስታወቂያ በደረሰው በ7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

13/ ነባር ባለሀብቶች የኩባንያቸዉን አክሲዮን የመጠቅለል ወይም ለቁጥጥር የሚያበቃ ግዢ ጥያቄ ሲቀርብላቸው፡-

ሀ) ሐሳቡን በሚገባ እንዲያስቡበት በቂ ጊዜ፤

ለ) የቀረበው ሐሣብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለመገምገም እንዲችሉ በቂ መረጃ፤

ሐ) ተግባራዊ ማድረግ እስከተቻለ ድረስ፣ በውሳኔ ሐሣቡ መሠረት ባለአክሲዮኖች ከሚያገኙት ማናቸውም ጥቅም ተጠቃሚ ለመሆን ምክንያታዊና ፍትሀዊ ዕድሎች፤ እና

መ) ከቀረበው ሃሳብ ጋር በተያያዘ ተመጣጣኝና ፍትሃዊ መስተንግዶ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## ክፍል አስራ አንድ
## የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ

### 86. <u>የህግ ቅርጽ</u>

የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ከሚከተሉት በአንዱ መልክ ሊቋቋም ይችላል፡-

1/ እንደ ጋርዮሽ ገንዘብ ያሉ የኢንቨስትመንት ኩባንያዎች፤

2/ የተወሰነ ኃላፊነት ያላቸው የሽርክና ማህበሮች፤ ወይም

3/ ባለስልጣኑ በጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥር መካተት አለባቸው ብሎ የሚወስናቸው ሌሎች በንግድ ህጉ የተደነገጉ አደረጃጀቶችና አወቃቀሮች፡፡

### 87. <u>የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አመዘጋገብ</u>

1/ ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ጋር የተያያዙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም ክፍልፋዮች በባለስልጣኑ ካልተመዘገቡ እና ምዝገባውም በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ለህዝብ ካልተገለፀ በስተቀር ሊሰራባቸው ወይም ሊሸጡ አይችሉም፡፡

2/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ምዝገባ ማመልከቻ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ ለባለስልጣኑ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) የማመልከቻ ቅጽ፣

ለ) ለባለስልጣኑ የሚከፈል የማመልከቻ ክፍያ፣

ሐ) የመመስረቻ እና መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም የመጨረሻ የቅርብ ጊዜ የፋይናንስ ሪፖርት፣ እና

መ) ሌሎች በደንብ ወይም በመመሪያ የተደነገጉ ወይም በባለስልጣኑ እንደሁኔታው የሚጠየቁ ሰነዶችና መረጃዎች፡፡

3/ ባለስልጣኑ ማመልከቻውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በቀረበው መሠረት መርምሮ ብቁ ሆኖ ካገኘው ፈንዱን ይመዘግባል፤ ይህንንም ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

4/ ባለስልጣኑ ስለ ጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች አይነት፣ በጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች ሥራ ላይ ሊውሉ ስለሚችሉ የኢንቨስትመንት ክፍልፋዮች፣ ስለሀብት አገማመት፣ ስለዋጋ ቁጥጥር፣ እና መረጃን ይፋ የማድረጊያ መስፈርቶችን የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፡፡

## 88. የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ

1/ ለጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ ሆኖ የሚያገለግል ማንኛውም ሰው ፈቃድ ለማግኘት፡-

ሀ) የስጋት አስተዳደር ዘዴዎች፣

ለ) የውስጥ ቁጥጥር፣

ሐ) የሒሳብ አሠራር ሥርዓት፣

መ) የድርጅት አስተዳደር፣

ሠ) ተገቢና ብቁ የሰውና የቴክኒክ ሀብት፣

ረ) ዝቅተኛ ተፈላጊ ካፒታል፣ እና

ሰ) ሌሎች በባለስልጣኑ መመሪያ የሚወሰኑ መስፈርቶች በተመለከተ ዝቅተኛ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

2/ ባለስልጣኑ፡-

ሀ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስትመንቶችን ለመምረጥ የሚካሄዱ የተገቢነት ጥናቶችን፤

ለ) የጋራ ኢነቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስተሮችን ጥቅም ማስጠበቅና በፍትሐዊነት የማስተናገድ መርሆዎችን መከተልን፤

ሐ) የጥቅም ግጭትን መለየትና የማስተዳደር፣ በተለይም ከተዛመደ አካል ጋር የሚደረግ ግብይይትን፤ እና

መ) የጋር ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራዎችን በሥርዓት መምራትና ማጠናቀቅን፤

በተመለከተ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድን ሥራ አከናዋኞች በየጊዜው ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ከአነስተኛ ደረጃዎች ጋር በመመሪያ ያወጣል፡፡

3/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኞች የፈንዱን ሀብቶች እና ከከፈንዱ አክሲዮኖችና ክፍልፋዮች ጋር የተገናኙ የገንዘብ ዝውውሮችን (ግዥና ሽያጭን) የሚመለከት መዝገቦችን መመዝገብና መያዝ አለባቸው፡፡

4/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኞች ማናቸውም አይነት በፈንዱ አስተዳደር ወይም መዋቅር ወይም በኢንቨስተሮች መብቶች ወይም በፈንዱ አሠራር ላይ የሚከሰቱ ጉልህ ለውጦችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

5/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ የራሱን ሀብት ከጋራ ኢንቨስትመንቱ ሀብት መለየት ይኖርበታል፡፡

6/ የደንበኛ ሀብት ከጋራ ኢንቨስትመንት ሥራ አከናዋኙ ጉዳትና ኪሳራ መጠበቅ አለበት፡፡

7/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኙ፤

ሀ) ክፍልፋዮችን ሽጦ የመዉጣት ጥያቄን ማሳካት የማይችል ከሆነ፤

ለ) ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዱ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ወይም ውሎች ወይም በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ጋር በሚቃረን መንገድ ክፍልፋዮችን ሽጦ መዉጣት ላይ እገዳ ከጣለ፤ ወይም

ሐ) ይህን አዋጅ ይጥሳል ተብሎ ከታመነ፤

ባለስልጣኑ ጣልቃ በመግበት የመፍትሔ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 89. <u>የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስተሮች መብት</u>

1/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አከናዋኝ፣ ሥራ ላይ ለማዋል በኢንቨስተሮች አስቀድመው መጽደቅ የማያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሆነው በኢንቨስተሮች መብት ላይ ጉልህ ለውጦች የሚያስከትሉትን ስራ ላይ ከማዋሉ በፊት ለኢንቨስተሮች ማስታወቅ አለበት፡፡

2/ በኢንቨስተሮች መብት ላይ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል ጉልህ ለውጥ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ኢንቨስተሮች፣ ከፈለጉ፣ ክፍልፋዮቻቸዉን ያለ ክፍያ እንዲሸጡ እድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

3/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስተሮች ክፍልፋያቸውን በመተዳደሪያ ደንብ፣ ወይም በመመስረቻ ፅሁፍ፣ ወይም በኮንትራት ወይም በደንበኛ ሳቢ መግለጫው መሠረት ያለምንም ቅድመ ማስታወቂያ ሽጠዉ መዉጣት ይችላሉ፡፡

## 90. <u>የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስትመንት አማካሪ</u>

ማናቸውም የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪ ሆኖ የሚያገለግል ሰው የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

1/ በኢንቨስትመንት አማካሪነት ለመስራት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ማግኘት፤

2/ የክፍልፋይ ባለድርሻዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዱ የሚመራባቸውን መመሪያዎችና አሠራሮች አክብሮ መንቀሳቀስ፤

3/ የኢንቨስትመንት ምክር በሚሰጥበት ጊዜ የግል ንብረቱን ለመጠበቅ ለሚተጋ ሰው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፤

4/ ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዱ ጋር የተያያዙ መደበኛ ሪኮርዶችን በፈንዱ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መዝግቦ መያዝ፤ እና

5/ በተጠየቀ ጊዜ እና በባለስልጣኑ መመሪያ መሠረት በየጊዜው ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ፡፡

## 91. የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ጠባቂ

1/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሀብት የጥበቃ ሥራ በሚያከናውን ሀብቱን በደንበኛ ሀብትነት ለይቶ በሚይዝ ራሱን በቻለ ሌላ ጠባቂ አካል ጥበቃ ሥር መሆን ይኖርበታል፡፡

2/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ጠባቂ በአሰራሩ ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ ገለልተኛ ሆኖ ሁልጊዜም ለኢንቨስተሮች ጥቅም የቆመ መሆን አለበት፡፡

3/ ባለስልጣኑ የጠባቂዉን፡-
ሀ) የፋይናንስ እና የማስተዳደር ብቃት፤ እና
ለ) የኢንቨስትመንት ፈንድ ሀብቶችን ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኙ፣ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪዉ እንዲሁም ከራሱ ሀብቶች ለይቶ የመጠበቅ ብቃቱን በተመለከተ መመዘኛዎችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 92. በጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ላይ የተጣሉ ገደቦች

1/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ የሚከተሉትን ተግባራት ከማከናወን የተከለከለ ነው፡-
ሀ) ብድር መስጠት፣
ለ) በባለስልጣኑ መመሪያ በወጡ መስፈርቶች እስከተፈቀደው መጠን ድረስ ካልሆነ በስተቀር፤ ፈንዱን ከሚያስተዳድረው ኩባንያ ወይም ከተቀጥላ ኩባንያዎቹ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛት፤ እና
ሐ) በባለስልጣኑ በወጣ መመሪያ ከተቀመጠው አግባብ ውጪ፣ የፈንዱ አማካሪ ለሕዝብ የማቅረብ ስራን ከሚመራበት ወይም የሽያጭ ወኪል ሆኖ ከሚያገለግልበት ማናቸውም ተቋም፣ ምንም አይነት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛት፡፡

2/ ማነኛዉም የጋራ ኢንቨስትምመንት ፈንድ ያለ ባለስልጣኑ ይሁንታ የኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪ ወይም ጠባቂ ሊሾም ወይም በሌላ ሊተካ አይችልም፡፡

3/ ባለስልጣኑ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪ ወይም ጠባቂ የመሾም ወይም የመተካት ማመልከቻ በደረሰዉ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ዉስጥ ውሳኔውን እና የውሳኔውን ምክንያት ያሳዉቃል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አማካሪ ወይም ጠባቂ የመሾም ወይም የመተካት ማመልከቻ ቀርቦለት ባለስልጣኑ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተቃዉሞ ካልገለፀ ማመልከቻዉ የባለስልጣኑን ይሁንታ እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል አስራ ሁለት
## የተከለከሉ የግብይት ተግባራት

### 93. ለህዝብ የተሰራጨ መረጃ

1/ ለዚህ አዋጅ አላማዎች፣ አንድ መረጃ ለህዝብ ተሰራጭቷል የሚባለው፡-

- ሀ) በባለስልጣኑ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ገበያ መመሪያዎች መሠረት ለኢንቨስተሮች እና ለአማካሪ ባለሙያዎች መረጃ ለመስጠት ተብሎ ከታተመ፣
- ለ) ተመዝግቦ ተይዞ በወጣ ህግ መሰረት ለህዝብ ዕይታ ክፍት ከሆነ፣
- ሐ) መረጃው፡-
  - 1) ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ፣ ወይም
  - 2) ከሰነደ ሙዓለ ንዋዩ አቅራቢ፣ጋር የተገናኘ ሆኖ ከሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጋር በተገናኘ ስራ ሊሰሩ በሚችሉ አካላት በቀላሉ ሊገኝ ከቻለ፣ ወይም
- መ) ለህዝብ እንዲያውቀው ከተደረገ መረጃ የተገኘ ከሆነ ነው፡፡

2/ መረጃው፡-

- ሀ) በጥንቃቄ በሚሰሩና የሙያው ብቃት ባላቸው ሰዎች ብቻ የሚደረስ፣
- ለ) በፍትሐዊና ተመጣጣኝ ክፍያ በቋሚ ደንበኝነት ወይም በክፍያ ለህዝብ የሚደርስ፣
- ሐ) በምልከታ ብቻ የሚገኝ፣ ወይም
- መ) ከኢትዮጵያ ውጭ ብቻ የሚታተም

ቢሆንም ለህዝብ እንደተሰራጨ ሊቆጠር ይችላል፡፡

### 94. የውስጥ አዋቂ መረጃ

1/ ለዚህ ክፍል አላማ ‹‹ውስጥ አዋቂ መረጃ›› ማለት ቀጥተኛ እና ግልጽ፣ ለህዝብ ያልተሰራጨ እና ለህዝብ ቢሰራጭ ኖሮ በማናቸውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዋጋ ላይ ጉልህ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡

2/ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከውስጠ አዋቂ መረጃዎች ጋር በተያያዘ ‹‹ዋጋቸው ተለዋዋጭ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች›› ናቸው የሚባሉት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እሴትን ጨምሮ መረጃው ለህዝብ ቢገለፅ በዋጋው ላይ ጉልህ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል ከሆነ ነው፡፡

## 95. ውስጥ አዋቂዎች

1/ ለዚህ ክፍል አላማ ‹‹ውስጥ አዋቂ›› ማለት የውስጥ መረጃ ያለው ሰው ነው፡፡

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አላማ አንድ ሰው፡-
- ሀ) ዳይሬክተር፣ ሰራተኛ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አቅራቢ ባለአክሲዮን በመሆኑ፤
- ለ) በሙያው፣ በስራ ቅጥሩ፣ በቢሮው ምክንያት መረጃውን የማግኘት ዕድል ያለው በመሆኑ፤ ወይም
- ሐ) ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆኑ የመረጃ ምንጭ በሆኑት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) በተጠቀሱት ሰዎች ሥር የሚወድቅ በመሆኑ

መረጃውን ያገኘ እንደሆነ ከውስጥ ምንጭ እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

## 96. የውስጥ አዋቂ ግብይት

1/ የውስጥ አዋቂ መረጃ ያለው ሰው፡-
- ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ከውስጥ አዋቂ መረጃ ጋር በተያያዘ ዋጋቸው ተለዋዋጭ ከሆኑ፤
- ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ግብይት ሊካሄድ እንደሚችል በማወቁ ወይም በቂ ምክንያት መኖሩን በማመኑ ሌላን ሰው ቢያውቅም ባያውቅም በውስጥ አዋቂው ይዞታ ሥር ካለ መረጃ ጋር በተያያዘ ዋጋቸው ተለዋዋጭ በሆኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም ከእነርሱ በሚመነጩ ሰነዶች እንዲገበያይ ካበረታታ፤ ወይም
- ሐ) ከተቀጠረበት ስራ፣ ከቢሮው ወይም ከሙያው ጋር ባልተያያዘ መንገድ መረጃውን ከገለፀ፤

በሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ መገበያየት አይፈቀድለትም፡፡

2/ አንድ ውል በዚህ አንቀጽ በተጠቀሱት ጥፋቶች ብቻ ፈራሽ ወይም የማይፈፀም ሊሆን አይችልም፡፡

3/ ባለስልጣኑ የውስጥ አዋቂ ንግድ ግብይትን ለመቆጣጠርና በበላይነት ለመከታተል ተጨማሪ ድንጋጌዎችን በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 97. የገበያ ሽፍጥ

አንድ ሰው ግብይቶችን በራሳቸው ወይም ከሌላ ማናቸውም ግብይት ጋር በማጣመር፡-

1/ ሌላ ሰው የተመሳሳይ ኩባንያን፣ ወይም የሌላ ተዛማጅ ኩባንያን፣ ወይም የተመዘገቡ ሌሎች መሰል ኩባንያዎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እንዲገዛ፣ ለመግዛት ቃል እንዲገባ፣ ወይም ከመሸጥ እንዲታቀብ ለመገፋፋት፣ በማሰብ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋን በሚጨምሩ፣ ወይም ሊጨምሩ፤

2/ ሌላ ሰው የተመሳሳይ ኩባንያን፣ ወይም የሌላ ተዛማጅ ኩባንያን፣ ወይም የተመዘገቡ ሌሎች መሰል ኩባንያዎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እንዲሸጥ፣ ወይም ስነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከመግዛት እንዲታቀብ ለመገፋፋት፣ በማሰብ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋን በሚቀንሱ፣ ወይም ሊቀንሱ፤ ወይም

3/ የተመሳሳይ ኩባንያን፣ ወይም የሌላ ተዛማጅ ኩባንያን፣ ወይም የተመዘገቡ ሌሎች መሰል ኩባንያዎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሌላ ሰው እንዲገዛ፣ እንዲሸጥ፣ ወይም ለመግዛት ቃል እንዲገባ፣ ወይም ስነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከመሸጥ፣ ከመግዛት እንዲታቀብ ለመገፋፋት፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ዋጋ ማረጋጋት፣ ወይም ሊያረጋጉ በሚችሉ በአንድ ኩባንያ ሰነደ መዓለ ንዋዮች ወይም በሌላ በይፋ በሚካሄድ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የሰነደ መዓለ ንዋዮች ግብይቶችን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መፈጸም አይችልም።

## 98. <u>የሀሰት ግብይት</u>

1/ ማንኛውም ሰው በመካሄድ ላይ ባለ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት በመጠንም ሆነ በዋጋ ላይ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ዕይታ እንዲኖር የሚፈጥር ወይም እንዲፈጠር የሚያደርግ ወይም ሌላ የተዛባ ሁኔታ ማድረግ የለበትም።

2/ በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ሰው፡-

- ሀ) በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጥቅም የባለቤትነት ለውጥን በማያስገኝ ሁኔታ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የመግዛት ወይም የመሸጥ ግብይት ከፈጸመ ወይም እንዲፈጸም ካቀረበ፤ ወይም
- ለ) በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለራሱ እንዲሸጥለት ባዘጋጀው ወይም ባቀረበው ዋጋ ለመሸጥ ካቀረበ፣ ወይም ከሱ ጋር የሚገበያየው ሰው በግልጽ በሚታይ ሁኔታ እንዲሸጥለት ያዘጋጀው ወይም ያቀረበው እኩል ብዛት ያላቸው ወይም እኩል ብዛት እንዳላቸወ በግልጽ ሊታወቁ የሚችሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ካቀረበ

ለዚህ ክፍል ዓላማ በመካሄድ ላይ ባለ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት እና ዋጋ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ዕይታ እንዲኖረው የማድረጉ ሁኔታ ተፈጥሯል።

## 99. <u>የተጭበረበረ ግብይት</u>

ማንኛውም ሰው፡-

1/ ሀሰተኛ፣ አሳሳችና፣ አታላይ መግለጫ ቃል በመስጠት፣ ትንበያ በመስጠት ወይም በማሳተም፤

2/ ወሳኝ መረጃ በመደበቅ፤ ወይም

3/ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች የሆነ መረጃ በመካኒካል ወይም በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ መሣሪያ በመቅዳት ወይም በማከማቸት

ሌላ ሰው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመሸጥ እንዲያመለክት፣ እንዲገዛ ወይም እንዲሸጥ መገፋፋት ወይም ለመገፋፋት መሞከር የለበትም፡፡

## 100. የሸፍጥ ዘዴዎችን መጠቀም

ማንኛውም ሰው፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፣ ከሌላ ሰው ጋር ከሚያደርገው ፈርሞ ከመግዛት፣ ከግዥ እና ከሽያጭ ግብይይት ጋር በተያያዘ፡-

1/ ሌላውን ሰው በማታለል ወይም ማንኛውንም አይነት መሣሪያ፣ ዘዴ፣ ወይም ረቂቅ መንገድን በመጠቀም፤ ወይም

2/ ሌላን ሰው በሚያጭበረብር ወይም በሚያታልል፣ ወይም ሊያታልሉ ወይም ሊየያጭበረብሩ በሚችሉ ድርጊቶችና ተግባራት ወይም አሠራር በመሠማራት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ሊገዛ ወይም ሊሸጥ አይችልም፡፡

## 101. ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫዎች

1/ ማንኛውም ሰው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ፣ ሌላ ሰው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም ሌሎች የተመዘገቡ ማናቸውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለመግዛት ቃል እንዲገባ፣ እንዲገዛ፣ ወይም እንዲሸጥ ለመገፋፋት አላማ፤ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ ባለበት እንዲቀጥል፣ እንዲጨምር፣ እንዲቀንስ ወይም እንዲረጋጋ ለማድረግ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግልጫ መስጠት የለበትም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣
አንድ ሰው፡-

ሀ) በተገለጸበት ጊዜና አኳኋን ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሀሰተኛና አሳሳች የሆነ እና ሰውየውም ሀሰተኛና የተዛባ መሆኑን የሚያውቀው ወይም አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ሊያውቀው የሚችል፤ ወይም

ለ) አንድ ወሳኝ ጉዳይ ቀሪ በመሆኑ ምክንያት ሀሰተኛና የተዛባ የሆነ፣ እና ሰውየውም ቀሪ በሆነው ወሳኝ ጉዳይ ምክንያት ሀሰተኛና የተዛባ መሆኑን የሚያውቀው ወይም አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ሀሰተኛና የተዛባ መሆኑን ሊያውቀው የሚችል

መግልጫ መስጠት የለበትም፡፡

## 102. የጆሮ ጠብ እና ሌሎች የግብይት አይነቶች

1/ የዋጋ ልዩነት ያለበት የደንበኛ ትዕዛዞችን በተመለከተ የውስጥ አዋቂ መረጃ ያለውና ትዕዛዞቹ መኖራቸውን ያወቀ እና በሚመለከተው ሰነደ መዓለ ንዋዮች ወይም በማናቸውም ኢንቬስትመንቶች በቀጥታ በሌላ ሰው አማካኝነት ለራሱ ግብይት የሚፈጽም ማንኛውም ህጋዊ ፈቃድ ያለው ሰው የደንበኛው ትዕዛዝ ከመፈጸሙ በፊት በዋጋ ልዩነቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

2/ ፈቃድ ያለው ሰው ከደንበኞቹ ቀድሞ መገበያየት ወይም በደንበኞቹ ፋንታ የዕለት ገበያ በተጋነነ መልክ ከፍ አድርጎ መዝጋት አይችልም፡፡

## 103. በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይት ስለሚጣሉ ገደቦች

ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ገደብ በተጣለባቸው ሰነደ ሙዓለ ነዋዮች ግብይት ማካሄድ አይችልም፡፡

# ክፍል አስራ ሶስት
# የካሣ ፈንድ

## 104. የካሳ ፈንድ ስለ ማቋቋም

1/ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት የገንዘብ ኪሣራ ለሚደርስባቸው ኢንቬስተሮች ካሣ የመስጠትን እና የመብት ጥያቄ ያልቀረበባቸውን የተሰበሰቡ የትርፍ ድርሻዎችን ሁኔታው ሲፈጠር ለተጠቃሚዎች የመክፈልን ዓላማዎች ያነገበ የካሳ ፈንድ (ከዚህ በኃላ ‹‹ፈንድ›› እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ውጭ ለኢንቨስተሮች የተሟላ ጥበቃ የሚያደርጉ ሌሎች ዝግጅቶች መኖራቸውን ካመነ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ግዴታዎች ነፃ ሊያደርገው ይችላል፡፡

3/ የካሣ ፈንዱ የገንዘብ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) ፈቃድ ባላቸው ሰዎች ለካሳ ፈንድ እንዲከፈል የሚጠየቅ ገንዘብ፤

ለ) የካሳ ፈንዱ ገንዘብን ኢንቨስት በማድረግ የሚገኝ ወለድና ትርፍ፤

ሐ) ግዴታቸውን መወጣት ባለመቻላቸው ኢንቨስተሮችን ለካሳ ክፍያ ከዳረጉ አካላት በባለስልጣኑ ወይም በባለስልጣኑ በተወከለ አካል የሚሰበሰብ ገንዘብ፤ ወይም

መ) በመንግሥት በፀደቀው መሠረት ለካሣ ፈንድ ዓላማዎች ከሌላ ማናቸውም ምንጭ
ከተገኘ ገንዘብ፡፡

4/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ሐ) የተጠቀሱትን ገንዘቦች ለማስከፈል የሚያስችል አዲስና ወቅታዊ መረጃ የሚያቀርብን ማንኛውንም ሰው ሊሸልም ይችላል፡፡ ሆኖም፤
   ሀ) ይህ ድንጋጌ በማንኛውም የባለስልጣኑ ሠራተኛ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤
   ለ) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈለው ሽልማት ከተገኘው ገንዘብ ከሦስት በመቶ ሊበልጥ አይችልም፤ እና
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ለ) የተጠቀሰው ሽልማት፣ የተገኘው ገንዘብ ወደ ፈንዱ ገቢ ከመደረጉ በፊት መከፈል አለበት፡፡

5/ በካሳ ፈንድ ውስጥ የተጠራቀመው ገንዘብ በባለስልጣኑ ኢንቨስት ሊደረግ ይችላል፡፡

6/ ከፈንዱ ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ጉዳዮች በሚኒስተሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ፡-
   ሀ) የፈንዱ አስተዳደር፤
   ለ) የፈንዱ ገንዘብ ኢንቨስት የሚደረግበት ፖሊሲ፤
   ሐ) በፈንዱ ውስጥ ሊኖር የሚችለው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን፣ እና ከዝቅተኛው መጠን ቢቀንስ መደረግ ያለበት ሁኔታ፤
   መ) የፈንዱን ግዴታዎች ለማሟላት ሊጣሉ ስለሚችሉ ክፍያዎች፤
   ሠ) በፈንዱ ላይ የይገባኛል ክስ የሚቀርብበት ሁኔታ፤ እና
   ረ) ፈንዱን ለማቋቋምና ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ ማናቸውም ጉዳዮች፡፡

## 105. <u>ከፈንዱ ስለሚፈጸሙ ክፍያዎች</u>

1/ ለፈንዱ የሚደረጉ መዋጮዎች እና ከፈንዱ የሚከፈሉ ክፍያዎች ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈጸማል፡፡

2/ በማንኛውም ፈቃድ ባለው ሰው ጥፋት ምክንያት ከካሳ ፈንዱ የሚደረግ ማናቸውም ክፍያ ለፈንዱ የሚከፈል/የሚመለስ እዳ ሆኖ፣ ባለስልጣኑም በማንኛውም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ የሚያስመልሰው ይሆናል፡፡

## 106. <u>የፈንዱ ሀብትና ዕዳ</u>

የፈንዱ ሀብቶች በዚህ ክፍል ለተመለከተው ዓላማ ሲባል ከሌሎች የባለስልጣኑ ንብረቶች ተለይተውና ተጠብቀው ይያዛሉ፡፡

# ክፍል አስራ አራት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 107. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>

1/ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ዕውቅና ሳይሰጠው እንደ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የሰራ ወይም እንደሚሠራ አድርጎ የተንቀሳቀሰ እንደሆነ፣ ከብር 100ሺ በማያንስና ከብር 150ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ12 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

2/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ፈቃዱ በባለስልጣኑ ሳይፀድቅለት በንግድ ሥራነት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ያቋቋመ ወይም የከፈተ እንደሆነ፣ ከብር 100ሺ በማያንስና ከብር 150ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ12 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

3/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ነዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ፈቃድ በሌለዉ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ተዛማጅ ውሎች ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የሌለዉ መሆኑን እያወቀ የተገበያየ እንደሆነ፣ ከብር 100ሺ በማያንስና ከብር 150ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ12 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

4/ ፈቃድ ከተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ውጭ ያለ ሌላ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ‹‹የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ›› ወይም ‹‹የአክሲዮን ገበያ›› ወይም ‹‹የተዛማጅ ውሎች ገበያ›› የሚል ስም፤ ወይም

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ከተጠቀሱት ስያሜዎች ከአንዱ ጋር በጣም ተቀራራቢ ስያሜ በመሆኑ ሊያታልል የሚችል ማናቸውም ስም፤

የወሰደ ወይም የተጠቀመ ወይም በየትኛውም ቦታ የለጠፈ ወይም ያሳየ እንደሆነ፣ ከብር 100ሺ በማያንስና ከብር 150ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

5/ ማንኛውም ሰው ያልተመዘገበ፣ በመንግስት ዋስትና ያልተሰጠው ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት በወጣ መመሪያ ከምዝገባ መስፈርቶች ግዴታ ነፃ ያልሆነ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ያወጣ እንደሆነ፣ ከብር 150ሺ በማያንስና ከብር 300ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ7 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

6/ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳይገኝ ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ተግባራት ተሰማርቶ የተገኘ እንደሆነ፣ ከብር 150ሺ በማያንስና ከብር 300ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ7 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

7/ ማንኛውም ሰው የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ፈቃድ ከተሰጣቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ወይም ካልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ውጭ ሲገበያይ የተገኘ እንደሆነ፣ ከብር 100ሺ በማያንስና ከብር 150ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ12 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

8/ ማንኛውም ሰው ማናቸውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ፈቃድ ከተሰጠው የገበያ አከናዋኝ ውጭ ሲገበያይ የተገኘ እንደሆነ፣ ከብር 50ሺ በማያንስና ከብር

100ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

9/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96 የተደነገገውን በመተላለፍ በውስጥ አዋቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተገበያየ እንደሆነ፣ ከብር 200ሺ. በማያንስና ከብር 350ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ7 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

10/ ማንኛውም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የተሿሚ እንደራሴነት ፈቃድ የሌለውን ሰው ዉክልና በመስጠት ቁጥጥር የሚደረግበትን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ወይም ተግባራትን ያሰራ እንደሆነ፣ ከብር 100ሺ. በማያንስና ከብር 150ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ12 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

11/ ማንኛውም ሰው የተሿሚ እንደራሴነት ፈቃድ ሳይኖረው እንደ ተወካይ ሆኖ ቁጥጥር የሚደረግበትን የካፒታል ገበያ አገልግሎት የሰጠ እነደሆነ፣ ከብር 100ሺ. በማያንስና ከብር 150ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ12 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

12/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት፣ ፈቃድ ለማግኘት ወይም ለማሳደስ ብሎ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በጽሑፍ፣ በቃል ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ሃሰተኛና የተዛባ መረጃ ያቀረበ ወይመ ሐሰተኛ መረጃ በማቅረብ ፈቃድ ያወጣ ወይም ያሳደሰ እንደሆነ፣ ከብር 150 ሺ. በማያንስና ከብር 300ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ7 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

13/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ባልተመዘገበ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለን ጥቅም የሚወክሉ አክሲዮኖችን፣ ክፍልፋዮችን ወይም ሌሎችን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለመግዛት፣ ለማስተላፍ ወይም ለማስወገድ ወይም ግዴታ ለመስገባት በመፈለግ ውል የተዋዋለ ውይም የፈጸመ ወይም እንዲፈጽሙ የጠየቀ፤ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ያልተመዘገበ የጋራ ኢንቨስትመን ፈንድ ያቋቋመ እና ያካሄደ እንደሆነ፣ ከብር 300ሺ. በማያንስና ከብር 500ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ10 ዓመት በማያንስና ከ20 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

14/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት አንድን ጉዳይ ለመከታተልና ለመመርመር የሚጠቅም ሰነድ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ያጠፋ፣ አስመስሎ ያቀረበ ፣ የደበቀ ወይም ያስወገደ፤ ወይም እንዲጠፋ፣ ተመሳስሎ እንዲሰራ፣ እንዲደበቅ ወይም እንዲወገድ ያስደረገ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፣ እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

15/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በገበያ ሽፍጥ፣ ወይ በሃሰተኛ ግብይት ወይም በማጭበርበር ግብይት ወይም በጆሮ ጠብ ንግድ የተሠማራ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 101 በተገለጸው መሠረት ማታለያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሌሎችን ሰዎች ያጭበረበረ ወይም ያታለለ፤

ሐ) ከደንበኞቹ ቀድሞ የተገበያየ፣ ወይም የዕለቱን ገበያ ዋጋ በተጋነነ ሁኔታ ከፍ አድርጎ የዘጋ ወይም በደንበኞቹ ስም ከሚገባው በላይ የተገበያየ፤ ወይም

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 102 በተደነገገው መሠረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ አንድ ሰው በሌላ ኩባንያ ውስጥ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም ሌሎች ማናቸውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለመግዛት እንዲፈርም፣ እንዲገዛ፣ ወይም እንዲሸጥ ለመገፋፋት በማሰብ፤ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ ባለበት እንዲቀጥል፣ እንዲጨምር፣ እንዲቀንስ ወይም እንዲረጋጋ ለማድረግ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ያወጣ እንደሆነ፤

ከብር 200ሺ. በማያንስና ከብር 350ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ7 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

16/ ማንም ሰው በውጤቱ እርግጠኛ ቢሆንም ባይሆንም ሌሎች ሰዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ እንዲገዙ ለመገፋፋት ወይም ባለአክሲዮኖችን ወይም ባለገንዘቦችን ለማታለል ወይም ለማጭበርበር በማሰብ ሀሰተኛ መሆኑን የሚያውቀውን የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ያዘጋጀ፣ ያሰራጨ ወይም ያሳተመ እንደሆነ፣ ከብር 200ሺ. በማያንስና ከብር 350ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ እና ከ7 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

17/ ማንኛውም ሰው፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 104(4) በተደነገገው መሠረት፡-

ሀ) ሽልማት ለማግኘት ብሎ ከባለስልጣኑ ሠራተኛ ጋር የተመሳጠረ፤

ለ) ከባለስልጣኑ እየሰራ ሳለ ሌሎች ሰዎች መረጃ እንዲያገኙ ያገዘ እና መረጃ የሰጠ፤ ወይም

ሐ) የተሳሳተ መረጃ የሰጠ፤

እንደሆነ፣ እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

18/ በዚህ አነቀጽ የተጠቀሱት ወነጀሎች የተፈጸሙት ህጋዊ ሰውነት ባለው ደርጅት የሆነ እንደሆነ፣ ድርጅቱ፡-

ሀ) እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ እስከ 500ሺ. ብር፤

ለ) እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ ከብር 500ሺ. በማያንስና ከብር 1 ሚሊዮን በማይበልጥ፤

ሐ) ከ5 እስከ 12 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ ከብር 500ሺ. በማያንስና ከብር 1.5 ሚሊዮን በማይበልጥ፤

መ) ከ7 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ ከብር 1 ሚሊዮን በማያንስና ከብር 2 ሚሊዮን በማይበልጥ፤ እና

ሠ) ከ10 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል፣ ከብር 1.5 ሚሊዮን በማያንስና ከብር 2.5 ሚሊዮን በማይበልጥ፤

የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

19/ በ ዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (18) ከተደነገገዉ ቅጣት በተጨማሪ፣ ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ህግ በጠያቂነት ወይም በራሱ ተነሳሽነት ድርጅቱ እንዲፈርስ ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ሊወስን ይችላል፡፡

20/ በዚህ አንቀጽ ከተደነገጉት ቅጣቶች በተጨማሪ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ያለ አግባብ የተገኘ ጥቅም እንዲወረስ ወይም እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

21/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከሚጣል መቀጮ የሚገኝ ገንዘብ እና የሚወረስ ወይም የሚመለስ ንብረት ለካሳ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል፡፡

## 108. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 107 መሠረት በወንጀል መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለስልጣኑ ራሱ በሚያደርገው የበላይ ክትትልና ምርመራ ላይ ተመሥርቶ ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በተላለፈ ሰው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ፣ ፈቃድ ሊሰርዝ ወይም ሊያግድ እና/ወይም የባለፈቃዱን ከፍተኛ ኃላፊዎችን ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ወይም እንዲታገዱ ትእዛዝ ሊሰጥ ወይም የገንዘብ ቅጣት ሊጥል ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ባለስልጣኑ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 109. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ ባለስልጣኑ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

3/ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የዚህን አዋጅ አንቀፅ 54 እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ከመንግስት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተያያዘ ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤትን እና ክፍያ ማጣራትና መፈፀምን የሚመለከቱ ደንቦችን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 110. የፈቃድ ዕድሳት

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም ፈቃድ፣ በባለስልጣኑ የሚጠየቀውን ክፍያ በመክፈል በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

## 111. የሠራተኞች አስተዳደር

የባለስልጣኑ የሥራ መሪዎች እና ሠራተኞች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የሚተዳደሩ ይሆናል፡፡

## 112. አለመግባባቶችን ስለመፍታት

1/ የዚህ አዋጅ ክፍል ሰባት (7) እንደተጠበቀ ሆኖ በካፒታል ገበያ ውስጥ በሚሳተፉ ወገኖች መካከል ይህን አዋጅ አስመልክቶ የሚነሳ ማንኛውንም የፍትሐብሔር ጉዳይ አለመግባባቶች በሽምግልና ይፈታሉ፡፡

2/ አለመግባባቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሽምግልና የማይቋጭ የሆነ እንደሆነ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲያልቅ ይደረጋል፡፡

3/ ከይግባኝ ጋር በተያያዘ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተሰጠው ውሳኔ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የመጨረሻ እና አስገዳጅ ይሆናል፡፡

4/ የግልግል ዳኞች ስለሚሾሙበት ሁኔታ እና ስለ ዳኞች ብቃት መስፈርት፣ ስለ ግልግል ዳኝነት አሠራር እና ከግልግል ዳኝነት ጋር የተያያዙ ወጭዎችን በተመለከተ ባለሥልጣኑ በሚያውጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 113. ስለተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

1/ የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2010 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 4 እና የአንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 (ለ) በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

2/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ህግ ወይም ልማድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 114. አዋጁ የሚጸናበት ቀን

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በአዲስ አበባ ቀን 2013 ዓ/ም
ሣህለወርቅ ዘውዴ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት